# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

82ኛ ዓመት ቁጥር 181 መጋቢት 1 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


## «በከተማዋ በቂ የጤፍ አቅርቦት የለም»

- ነጋዴዎች

## «የጤፍ ዋጋ መናር ፈተና ሆኖብናል»

- የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች

## «የኑሮ ውድነት ጉዳይ የእኛ ኃላፊነት አይደለም»

- የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር

**ሳሙኤል ወንደሰን እና አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- በቂ የጤፍ አቅርቦት ባለመኖሩ እና በጤፍ ዋጋ ላይ ከፍተኛ ጭማሪ በመደረጉ ጤፍ ገዝተን እንጀራ መብላት አልቻልንም ሲሉ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ገለጹ።

ጤፍ ሲገዙ ያገኘናቸው የአዲስ አበባ ነዋሪ ወይዘሮ አረጉ ጥፍጤ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የጤፍ ዋጋ በጣም ጨምሯል፤ በወፍጮ ቤቶች ጤፍ የለም። በአንዳንድ ወፍጮ ቤቶች ቢገኝም እንደጤፉ ዓይነት እስከ ስምንት ሺህ አምስት መቶ ብር ድረስ እየተሸጠ ይገኛል።

25 ኪሎ ጤፍ በሁለት ሺህ ብር ገዝቻለሁ ያሉት ወይዘሮ አረጉ፤ ነገር ግን ዋጋው በዚህ ሁኔታ የሚቀጥል ከሆነ «ጤፍ ገዝቼ እንጀራ የምበላ አይመስለኝም» ሲሉ ገልጸዋል። በተጠቀሰው ዋጋ ለመግዛት ምርቱን ማግኘት እንዳልተቻለ ጠቅሰው፤ መንግሥት ጉዳዩን ትኩረት ሰጥቶ ሊያየው ይገባል ብለዋል።

የአዲስ አበባ ነዋሪው አቶ መሀመድ ጀማል በበኩላቸው፤ በገበያው ላይ በቂ ጤፍ ባለመኖሩ ኅብረተሰቡ ሳያልቅ እንግዛ እየተባባለ ነው። በወፍጮ

«በከተማዋ በቂ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ፡ እዮብ ተፈራ

# በሶማሌ ክልል በተከሰተ ድርቅ 3 ነጥብ 7 ሚሊዮን ዜጎች ለተረጂነት ተጋልጠዋል

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በሶማሌ ክልል ባሉ 11 ዞኖች በተከሰተው ድርቅ 3 ነጥብ 7 ሚሊዮን ሕዝብ ለተረጂነት መጋለጡን የክልሉ ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ አስታወቀ።

የሶማሌ ክልል ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ አቶ አብዱልቃድር ረሺድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ ድርቁ በክልሉ ሁሉም ዞኖች የተከሰተ ሲሆን አደጋው በሸበሌ፣ በዳዋና በአፍዴር ዞኖች የከፋ ሆኗል። በድርቁ ምክንያት ለተረጂነት ከተጋለጡት ከ3 ነጥብ 7 ሚሊዮን ዜጎች አሁን ላይ እርዳታ እያገኙ ያሉት 1 ነጥብ 3 ሚሊዮን ያህሉ ብቻ ናቸው። 2 ነጥብ 4 ሚሊዮን ዜጎች አስቸኳይ እርዳታ ያስፈልጋቸዋል።

እስካሁን ባለው ሁኔታ በዳዋ ዞን ብቻ ግመሎችን

በሶማሌ ክልል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል














## ከዓለም ባንክ

### በተገኘ የ600 ሚሊዮን ዶላር ድጋፍ የሥርዓተ ምግብ ማጠናከሪያ ፕሮግራም ይፋ ተደረገ

ገጽ 4

## 20 ኢንቨስተሮች በስኳር ኢንዱስትሪ ለመሰማራት ፍላጎት አሳይተዋል

ገጽ 4







# ከኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚወጣን ቆሻሻ ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ ተፈረመ

**ታደሰ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ከፓርኮች የሚወጣን ቆሻሻ ጥቅም ላይ ለማዋል ከጃፓን የቴክኖሎጂ ኩባንያዎች ጋር የመግባቢያ ሰነድ ተፈረመ።

የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ዳይሬክተር አቶ አክሊሉ ታደሰ፤ የስምምነት ሰነዱን አስመልክተው ባደረጉት ንግግር የመግባቢያ ሰነዱ ከፓርኮች የሚለቀቀውን የቆሻሻ ዝቃጭ ለመልሶ ግልጋሎት ለማዋል የሚያስችል ስምምነት ነው ብለዋል።

ተቋሙ ከኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚወጣን ደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ ለተለያዩ ግልጋሎቶች ለማዋል ‘ሰንቴክኖ’ እና ‘ታናሜ’ ከተሰኙ ሁለት የጃፓን የቴክኖሎጂ ኩባንያዎች ጋር በቅንጅት ለመሥራት መዋዋሉን ገልጸዋል።

ዳይሬክተሩ በስምምነቱ እንደገለጹት፣ ከኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚወጣን ቆሻሻ ለተለያዩ ግልጋሎቶች ለማዋል ሲሠራ ቆይቷል። መንግሥትም ኢንዱስትሪ ፓርኮችን ከማስፋፋትና የሚለቀቀውን ቆሻሻ መልሶ ጥቅም ላይ ለማዋል የተጠናከረ ሥራ እየሠራ ነው ።

ተቋሙ ከሁለቱ የጃፓን የቴክኖሎጂ ኩባንያዎች ጋር የተፈራረመው የመግባቢያ ሰነድ ኢትዮጵያ ከኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚወጣ ቆሻሻን ለማስወገድ የምታወጣውን ከፍተኛ የሆነ በጀት ለማስቀረት ትልቅ ሚና ይጫወታል ብለዋል።

ዓለም የደረሰበትን ቴክኖሎጂ ባሉን ፋብሪካዎች በመጠቀም ከፓርኮች የሚወጣን ደረቅ ቆሻሻ ወደ ማዳበሪያነትና ፈሳሽ ቆሻሻዎችን ወደ ኃይል ማመንጫነት በመቀየር ለመልሶ ግልጋሎት የማዋል የሙከራ ሥራ በሁለት ሦስት ዓመታት ውስጥ እንደሚካሄድ ገልጸዋል።



ከፓርኮች የሚወጣውን ደረቅ ቆሻሻ መልሶ ጥቅም ላይ የማዋል የሙከራ ሥራ የሚጀመረው በሀዋሳ ኢንዱስትሪያል ፓርክ መሆኑን የገለጹት ዳሬክተሩ፤ ከሁለት ወራት በኋላ ሙከራው የሚጀመር ሲሆን ወደ ሌላ ፓርኮች እንደሚስፋፋም አመላክተዋል።

የሰንቴክ ቴክኖሎጂ ኩባንያ ዋና ዳይሬክተር ማሳሮ ካኒኮ በስምምነቱ እንደተናገሩት፤ በሀዋሳ ኢንዱስትሪያል ፓርክ ኩባንያው አስፈላጊ የሆነውን ጥናት አጥንቶ በማጠናቀቅ ወደ ሙከራ ሥራው ለመግባትና ቆሻሻ ለመልሶ ግልጋሎት ለማዋል ይሠራል ብለዋል።

የካናቤ የቴክኖሎጂ ኩባንያ ዋና ሥራ አስኪያጅ ዮሽያሱ ታናቤ በበኩላቸው፤ ኩባንያው ቴክኖሎጂን በመጠቀም ከኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚወጣን ቆሻሻ ጥቅም ላይ ለማዋል የበኩሉን ድርሻ እንደሚወጣ ገልጸዋል።



አቶ ሐብታሙ ኃይለሚካኤል

## ከድርጅቱ ሰርቨር ላይ አራት ሚሊዮን የሚጠጉ ሰነዶች እንዲጠፉ ተደርጓል

**- ለመንግሥት ልማት ድርጅቶች ሂሳብ አያያዝ ልዩ ትኩረት ተሰጥቷል**

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅት ከሰርቨሩ ላይ እስከ አራት ሚሊዮን የሚደርሱ ሰነዶች ሆንተብሎ እንዲጠፉ ተደርጎ እንደነበርና ይህም ለሂሳብ ሥራ አስቸጋሪ ሁኔታ መፍጠሩ ተገለፀ። የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የሂሳብ አያያዝም ልዩ ትኩረት እንደተሰጠው ተጠቁሟል።

የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር አቶ ሐብታሙ ኃይለሚካኤል በተለይም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅት ከሰርቨሩ ላይ የነበረው ዳታ ሙሉ ለሙሉ እንዲጠፋ ተደርጓል። ይህም ሆንተብሎ መረጃው እንዲጠፋ የተደረገበት ነው። በዚህም እስከ 4 ሚሊዮን የሚጠጋ ሰነድ በእጅ አንድ በአንድ ሰብስቦ በመመዝገብ ሂሳባቸውን ወቅታዊ ለማድረግ እየሠሩ ነው። አንዳንዶቹ የልማት ድርጅቶች ደግሞ ሂሳባቸውን በወቅቱ መዝጋት ብቻ ሳይሆን በዘመናዊ አሠራር እያዘመኑት ነው። ይህም በመሆኑ የተፈለገውን ውጤት ለማስመዝገብ አስቸጋሪ መሆኑን አስገንዝበው፤ በአሁኑ ወቅት ችግሮቹን ለማረም ልዩ ትኩረት እንደተሰጠው አመልክተዋል።

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለፃ፤ ‹‹አንድ ተቋም ትክክለኛ የፋይናንስ ተቋም ነው የሚባለው የፋይናንስ ሁኔታው ሲታወቅ ነው። ስለዚህ የእኛ ትልቁ ሥራ የነበረው የኮርፖሬት ፋይናንስና አስተዳደር ሥርዓት መዘርጋት ነው›› ብለዋል። በመሆኑም የልማት ድርጅቶች ወቅታዊ ሂሳብ እንዲኖራቸው በትኩረት ሠርተናል፤ የኦዲት ባክሎክ እንዲዘጋም ተደርጓል ነው ያሉት።

ቀደም ሲል በከፍተኛ ኪሳራ እና ውጥንቅጥ ውስጥ ከነበሩ የልማት ድርጅቶች መካከልም ኢትዮ ኢንጂነሪንግ አንዱ መሆኑንና በአሁኑ ወቅት በዚህ ተቋም ዘመናዊ የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መዘርጋቱን የጠቆሙት አቶ ሐብታሙ፤ ኢትዮ-ኢንጂነሪንግ እስከ 2012 ዓ.ም ሂሳቡን እየዘጋና እያፀዳ ነው። የኋላ የሂሳብ ታሪኩን እየዘጋ 2013 እና 2014 ዓ.ም ይቀረዋል። በመሆኑም ተቋሙ ቀድሞ ከነበረበት ሂሳብ መያዝና ሰነድ መመዝገብ ከማይቻልበት ታሪክ ወጥቷል። ከኋላ ታሪኩ የተነሳ የኦዲት ሁኔታው ችግር ያለበት ቢሆንም ችግሮችን ለማስተካከል እየሄደ መሆኑንም አረጋግጠዋል።

የኢትዮ-ኢንጅነሪንግ ግሩፕ በቀድሞ ስሙ ሜቴክ የተሰኘው ተቋም ራሱ ብቻ ሳይሆን አገርን ይዞ ሊጠፋ የነበረ ተቋም መሆኑን አብራርተው፤ ትልልቅና በቢሊዮን የሚቆጠሩ ፕሮጀክቶችን እንዲያስተዳድር ተደርጎ ነበር። አቅምና ብቃት ካለመኖሩም በተጨማሪ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ሳይዘረጋ ቢሊዮኖች የፈሰሱበትን ፕሮጀክት ለማስተዳደር ሲንቀሳቀስ ነበር። የውስጥ ቁጥጥር፤ የማኔጅመንት፣ የሀብት አስተዳደር የሌለው፤ ሥራው በግልጽ የማይታወቅ እና ሌሎች ችግሮች ነበሩበት። አሁን ላይ የአመራር፣ አሠራርና አደረጃጀት ችግሮችን ለማስተካከል ከፍተኛ የሆነ የውስጥ ኦዲት ሥርዓት እየተዘረጋ መሆኑን አስገንዝበዋል።





## ፎረሙ ዘላቂ ሰላም በማረጋገጥና በመልሶ ግንባታ ላይ በትኩረት ይሠራል

**ሄርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- ተጋሩ ኢትዮጵያውያን ለዘላቂ ሰላም ፎረም ዘላቂ ሰላምን ለማረጋገጥ እና በጦርነት የወደሙ አካባቢዎችን መልሶ ማልማት ላይ ትኩረት ሰጥቶ እንደሚሠራ ገለጸ።

ፎረሙ በትናንትናው ዕለት ሲመሰረት ጋዜጣዊ መግለጫ የሰጡት የማህበሩ ሥራ አስፈፃሚ አቶ ከበደ አሰፋ እንዳስታወቁት፤ ሕዝብና አገርን ዓላማ የሚያደርግ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ፣ ሲቪክ ማኅበር፣ የንግድ ማኅበረሰብ፣ ዳያስፖራ ማህበር እና ግለሰቦችም ጭምር በአንድነት በመሆን እና ልዩነታቸውን ወደ ጎን በመተው በአገርና ሕዝብ ላይ የደረሰው ችግር ለመፍታት ከሁሉም አካላት ጋር ተባብሮ ይሠራል።

ፎረሙ ዘላቂ ሰላምን ማረጋገጥ እና በጦርነት የወደሙ አካባቢዎች መልሶ ማልማት ዋና ዓላማው እንደሆነ የገለጹት ሥራ አስፈፃሚው፤ ለዚህም ሕዝቡ ከችግር እንዲላቀቅ ተባብሮ መሥራት እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

በአገሪቱ የሰሜኑን ጦርነት ተከትሎ የመጣው ከፍተኛ ኪሳራ፣ በሕዝቦች መካከል የተፈጠረው መጠራጠርና ቅራኔ፣ ላለፉት ዓመታት የተሰበከው መከፋፈል ለግዛት አንድነት የሚፈትኑ ችግሮች በማስከተሉ ችግሩን ለመፍታት በቅርቡ የተደረገው የሰላም ስምምነት ቀጣይነት እንዲኖረው እንደሚሠራም አብራርተዋል።

እኛ ኢትዮጵያውያን እንደ ዜጋ የሚያኖር ሰፊ አገር ስላለን ጠንካራ አደረጃጀት መፍጠር ይኖርብናል ያሉት ሥራ አስፈፃሚው፤ ሁሉም የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ለሁሉም እኩል በመቆምና ጠንካራ አንድነት በማሳየት ተባብሮ እንዲረዳዳ ጥሪ አቅርበዋል።

ኢትዮጵያዊነት የተጋሩ ግብ መሆኑን ጠቅሰውም፤ በተለያየ አቅጣጫ ተደራጅተው ኢትዮጵያዊነትን አደጋ ላይ የጣሉ አካላትንና ፅንፈኛ ፖለቲከኞችን በተደራጀ መልኩ ልንታገላቸው ይገባል ብለዋል።

ተጋሩ ኢትዮጵያውያን ለዘላቂ ሰላም ፎረም የሚያከናውናቸው ዝርዝር ተግባራት ያቀረቡት የፎረሙ ኦዲተር ሙሉጌታ ሓድጉ በበኩላቸው፤ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት እንዲጠናከር ማስተባበር እና በጦርነቱ ምክንያት የተፈናቀሉ ዜጎች ወደ ቀያቸው የመመለስ ሥራ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ መሆኑን ጠቅሰዋል።

በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ አደጋ ምክንያት ለሚከሰቱ የማኅበረሰብ ችግሮች ፎረሙ ድርሻውን ይወጣል ያሉት አቶ ሙሉጌታ፤ በሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ዙሪያ ማህበራዊ ኃላፊነት እንዲፈጠር ይሠራል ብለዋል።



አቶ ሰለሞን ሶካ

## ተቋሙ ከ270 ሚሊዮን ብር በላይ የኢኮኖሚ ኪሳራን ታድጓል

**ታደሰ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ስድስት ወራት ወደ አገር እንዳይገቡ በተከለከሉ የደህንነትና የመገናኛ ቴክኖሎጂ መሣሪያዎች ላይ በተደረገ ቁጥጥር ከ270 ሚሊዮን ብር በላይ ኪሳራን መታደግ እንደተቻለ ተገለጸ።

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ሰለሞን ሶካ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2015 የመጀመሪያው ግማሽ በጀት ዓመት ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት ፈቃድ ከተጠየቀባቸው ሁለት ሺህ 158 የተለያዩ ቴክኖሎጂዎች ውስጥ 297 የሚሆኑት የደህንነትና የመገናኛ ቴክኖሎጂ ምርቶች በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊና በፖለቲካዊ ዘርፍ አደገኛ የደህንነት ስጋት የሚያስከትሉ በመሆናቸው እንዳይገቡ ተደርገዋል።

ቁጥጥሩ በተለያዩ ኬላዎች የሚደረግ ሲሆን በተለይ በቶጎጫሌ ጉምሩክ ጣቢያ በተደረገ ፍተሻ በአገር ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ የቴክኖሎጂ መሣሪያዎች ተይዘዋል። በፍተሻ ኬላው ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ የተከለከሉ የደህንነትና የመገናኛ መሣሪያዎች በመያዛቸው በአገር ኢኮኖሚ ላይ ሊደርስ የነበረውን ከ270 ሚሊዮን ብር በላይ ኪሳራ ማዳን መቻሉን ገልጸዋል።

የተከለከሉ የመረጃና የመገናኛ ቴክኖሎጂ ምርቶች ቁጥጥርና ፍተሻ ሳይደረግባቸው ወደ አገር ውስጥ ገብተው ጥቅም ላይ ቢውሉ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ እና በፖለቲካዊ ዘርፍ ላይ ጉዳት ያደርሳሉ ሲሉ አቶ ሰለሞን አብራርተዋል።

በመሆኑም የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ከአገር የሚወጡ እና ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ የመረጃና የመገናኛ ቴክኖሎጂ ምርቶች በመቆጣጠር በአገር ደህንነት ላይ የሚደርሰውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ የአደጋ ስጋት ለመቀነስ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየሠራ መሆኑን ዋና ሥራ አስኪያጁ ተናግረዋል።

የመረጃና የመገናኛ ቴክኖሎጂ መሣሪያዎች በየጊዜው ተለዋዋጭ እና አዳዲስ ሲሆኑ በቀላሉ የማይለዩና ለተለያዩ ሕገወጥ ተግባራት ውለው ለአገር የደህንነት ስጋት ከመሆናቸው በፊት በአገሪቱ መግቢያ እና መውጫ ላይ ባሉ ኬላዎች የሚደረገው ድንገተኛና አካላዊ የመስክ ፍተሻ ተጠናክሮ መቀጠሉን ገልጸዋል።

ቁጥጥሩ የሚካሄደው በሰባት ካታሎግ ተከፍሎ ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ በወታደራዊ የቅኝት መሣሪያዎች፣ በመረጃ አነፍናፊ አንቴናዎች፣ ለአፈና ሥራ የሚውሉ ጃመሮች፣ የሌዘር እና የሴንሰር መሣሪያዎች፣ ወታደራዊ ራዲዮኖችና ራዳሮችን በመጠቀም ከፍተኛ የፍተሻ ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉ አብራርተዋል።

የአገርን ደህንነት ስጋት ውስጥ ይጥላሉ ብሎ ተቋሙ ወደ አገር እንዳይገቡ ክልከላ የጣለባቸው የደህንነትና የቴክኖሎጂ መሣሪያዎች በፍቃድና በውል እንዲገቡ መደረጉን የገለፁት አቶ ሰለሞን በየቀኑ ክትትልና ቁጥጥር ይደረግባቸዋል ብለዋል።

# በወረዳው በበጋ መስኖ ስንዴ 52 ሺህ ኩንታል ምርት ይጠበቃል

**ሄለን ወንድምነው**



አዲስ አበባ፡- ከበጋ መስኖ ልማት ሥራዎች 52 ሺህ ኩንታል የስንዴ ምርት እንደሚጠበቅ በሰሜን ወሎ ዞን የግዳን ወረዳ ግብርና ጽሕፈት ቤት አስታወቀ።

የግዳን ወረዳ ግብርና ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ካሳሁን ሞላ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በአጠቃላይ በወረዳው በበጋ መስኖ ልማት ከተሸፈነው 1ሺህ 936 ሄክታር መሬት 52 ሺህ ኩንታል ስንዴ ምርት ይጠበቃል።

በወረዳው በሚገኙ 12 ቀበሌዎች ላይ በ52 ክላስተር የለማውን ስንዴ የመንከባከብ ሥራ እየተከናወነ ይገኛል፤ ከሰኔ 2015 ዓ.ም የመጀመሪያው ሳምንት አንስቶ ሰብሉን የመሰብሰብ ሥራ ይጀመራል ብለዋል።

የወረዳው አርሶ አደሮች ከዚህ በፊት በተበጣጠሰ መንገድ ስንዴን ሲያመርቱ እንደነበር ያስታወሱት ኃላፊው፤ አሁን ላይ በተደራጀ መልኩ በክላስተር ልማት እንዲጠቀሙ መደረጉን አስረድተዋል።

ለወረዳው የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ሥራ የሰሜን ወሎ ዞን ግብርና መምሪያ ምርጥ ዘርና ከ2 ሺህ ኩንታል በላይ ማዳበሪያ አቅርቧል። በተጨማሪ ለግብርና ባለሙያዎች ስልጠና በመስጠት በየጊዜው ክትትል እየተደረገ ይገኛል ሲሉ አስታውቀዋል።

አቶ ካሳሁን እንደገለጹት፤ አርሶ አደሮቹ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን እንዲጠቀሙና ዘመናዊ የአስተራረስ ዘዴን እንዲከተሉ የቀበሌ ግብርና ባለሙያዎች በየጊዜው ክትትል በማድረግ ላይ ናቸው። ለቀበሌ ግብርና ባለሙያዎችና ለመስኖ ውኃ አዳዮች ለሰብሉ የሚያስፈልገውን ሳይንሳዊ የመስኖ ውኃ አጠቃቀም በተመለከተ ስልጠና መሰጠቱን አስታውቀዋል።

አርሶ አደሮቹ በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት የተሻለ ልምድ እንዲኖራቸው በማድረግ መቼ መዝራት እንደሚገባቸው፤ ለሰብሉ ምን ምን ግብዓቶች እንደሚያስፈልጉት በመለየት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በሚቻልበት ሁኔታ ላይ የግንዛቤ ፈጠራ ሥራዎች ቀድመው እንደተሠሩም አቶ ካሳሁን ተናግረዋል።

የግዳን ወረዳ አስተዳዳሪ አቶ ታምራት ንጋቱ በበኩላቸው፤ ወረዳው ከፍተኛ የመስኖ ውሃ ክምችት ያለበት በመሆኑ አርሶ አደሩ ዘመናዊ የመስኖ ውኃ አጠቃቀም እንዲከተል ከማድረግ አንጻር በትኩረት እየተሠራ እንደሚገኝ አስረድተዋል።

አርሶ አደሮች በክላስተር በተደራጀ የመስኖ ልማት በስፋት በመሳተፋቸው የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ ባለፈ ምርቱን ለገበያ በማቅረብ ኢኮኖሚያቸውን እንደሚያሳድጉ ይጠበቃል ብለዋል።

በቀጣይ በወረዳው ያለውን የመስኖ የውኃ አማራጮች ዘመናዊ የውኃ መሠረተ ልማቶች ገንብቶ ከመጠቀም አኳያ ድክመት እንዳለ አንስተዋል።

እስካሁን ባለው የዘመናዊ የመስኖ ውኃ መስመር ዝርጋታ ስድስት ቀበሌዎች ተደራሽ ሲሆኑ፤ ሊለማ የሚችለው አካባቢ፣ ሊያለማ የሚችለው የውኃ መጠንና የአርሶ አደሮችን ፍላጎት ታሳቢ ባደረገ መልኩ በቀጣይ ስምንት ቀበሌዎች ላይ የመስኖ ልማት ሥራውን ለማስፋፋት የሚያስችል ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን አስታውቀዋል።

# ዲጂታል የእንግሊዝኛ ቋንቋ መማሪያ መተግበሪያ ደረጃና ተደራሽነት ሊሻሻል ነው

**መክሊት ወንድወሰን**

አዲስ አበባ፡- ዲጂታል የእንግሊዝኛ ቋንቋ መማሪያ መተግበሪያ ተገልጋዮችን በዕውቀት ደረጃ በመለየት ግልጋሎት መስጠት እንደሚጀምር እና ተደራሽነቱን ለማስፋት እንደሚሠራ ትምህርት ሚኒስቴር አስታወቀ።

በትምህርት ሚኒስቴር የሶፍትዌር ቀማሪ አቶ አለምሁሉ አወቀልኝ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቆይታ እንደተናገሩት፤ ዲጂታል የእንግሊዝኛ ቋንቋን ያለምንም የበይነ መረብ ክፍያ ለማስተማር የሚያስችል መተግበሪያ ከወራት በፊት ይፋ ሆኗል። ይህ መተግበሪያ ሁሉንም የማኅበረሰብ ክፍል የሚያሳትፍ ሲሆን ብዙዎች ቋንቋው ላይ የሚኖራቸውን ክፍተት የሚሞላ ነው።

ይሁንና ትምህርቱን ሲወስዱ ቋንቋ ላይ ያላቸውን ደረጃ በለየ መልኩ ትምህርቱ እየተሰጠ አልነበረም። በቀጣይ ግን መምህራንን እና ተማሪዎችን በመለየት እንደየክፍል ደረጃቸውና የቋንቋ ዕውቀታቸው ግልጋሎት እንዲሰጥ ይደረጋል።

በመተግበሪያው ከክፍል ልየታውና የዕውቀት አቅም ባሻገር ተደራሽነቱን የማስፋት ሥራ እንደሚሠራ የገለጹት ባለሙያው፤ ተማሪዎች የሚማሯቸው ትምህርቶች በእንግሊዝኛ ቋንቋ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ያሉባቸውን የቋንቋ ክፍተቶች ለመሙላት ከፍተኛ ሚና እንደሚኖረው ገልጸዋል። መተግበሪያው በትምህርት ሚኒስቴር የቴክኖሎጂ ባለሙያዎች የተዘጋጀ ሲሆን፤ ከተማሪዎችና መምህራን በተጨማሪ ሁሉም የማኅበረሰብ አካል ሊጠቀምበት እንደሚችል ተናግረዋል።



አቶ አለምሁሉ አወቀልኝ

በትምህርት ቤቶች የሚሰጠውን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት የበለጠ በማጠናከር በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የተማሪዎችን የመረዳት አቅም ለማሻሻል ወሳኝ ሚና እንደሚኖረው አክለው ተናግረዋል።

ከተለያዩ አገራት የተውጣጡ በጎ ፈቃደኛ የእንግሊዝኛ መምህራንን እና የዳያስፖራ አባላትን በማሳተፍ መተግበሪያው ሥራ መጀመሩን ተናግረው፤ መተግበሪያው ተግባራዊ በመሆኑ ለመምህራን እና ለተማሪዎች ተጨማሪ አቅም እየፈጠረ መሆኑን ጠቅሰዋል። በይነ መረብ (ኢንተርኔት) በማይደርስባቸው አካባቢዎች ተማሪዎች በየትምህርት ቤቶቻቸው በመተግበሪያው የሚተላለፉትን ፕሮግራሞች እንዲያገኙ ይደረጋል ሲሉም ተናግረዋል።

የመማሪያ መጻሕፍትን ጨምሮ የተለያየ ይዘት ያላቸው የእንግሊዝኛ ትምህርቶችን በመተግበሪያው አማካኝነት በተለያየ የክፍል ደረጃ ለማቅረብ እየተሠራ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ዓለምሁሉ፤ ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር በመነጋገር ከአገልግሎት ክፍያ ነፃ በመደረጉ ተማሪዎች ተንቀሳቃሽ ምስሎችን እንደልባቸው እንዲያዩ ከፍተኛ ዕድል እንደፈጠረላቸው ጠቁመዋል። አሁን ባለው መረጃ የተማሪዎች የማየትና ትምህርቱን የመከታተል አቅማቸው እየጨመረ መሆኑን አስረድተዋል።

ተማሪዎችና መምህራን እንዲሁም ቀሪው የማኅበረሰብ ክፍልም የእንግሊዝኛ ቋንቋን ለመማርና ለማሻሻል እንዲጠቀምበት መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

# ከዓለም ባንክ በተገኘ የ600 ሚሊዮን ዶላር ድጋፍ የሥርዓተ ምግብ ማጠናከሪያ ፕሮግራም ይፋ ተደረገ

**ሞገስ ፀጋዬ**

ድሬዳዋ፡- ከዓለም ባንክ በተገኘ የ600 ሚሊዮን ዶላር ድጋፍ የምግብ ሥርዓት ማጠናከሪያ ፕሮግራም ይፋ ሆኗል። በቀጣይ ሰባት ዓመታት የግብርናውን ዘርፍ በማዘመን የምግብ ሥርዓትን ለማሳደግ እንደሚሠራ ግብርና ሚኒስቴር አስታውቋል።

የግብርና ሚኒስትር ዶክተር ግርማ አመንቴ ፕሮግራሙ ይፋ በተደረገበት በትናንትናው ዕለት ባደረጉት ንግግር እንደገለጹት፣ የዓለም ባንክ የኢትዮጵያ ግብርና እንዲዘምን ፍላጐት ስላለው ለዘርፉ የተለያዩ ድጋፎችን ሲያደርግ ቆይቷል። አሁን የተገኘው የ600 ሚሊዮን ዶላር ድጋፍ ኢትዮጵያ ከምትከተለው የግብርና ስልት ጋር የሚጣጣም በመሆኑ ግብርናውን ለማጠናከር ይውላል። ለአርሶ አደሮች ያለው ጠቀሜታም ከፍተኛ ነው።

ፕሮግራሙ በዘጠኝ ክልሎች፤ በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የሚተገበር ይሆናል ያሉት ሚኒስትሩ፤ በተመረጡ 181 ወረዳዎችና ከአራት ሺህ በላይ ቀበሌዎች የሚተገበር እንደሚሆን አስረድተዋል። የተገኘውን ሀብት በትብብር በመሥራት ውጤታማ እንዲሆንና የአርሶ አደሩን ሕይወት መለወጥ እንደሚገባ



ዶክተር ግርማ አመንቴ

አስገንዝበዋል።

እንደ ዶክተር ግርማ ገለፃ፤ ግብርና ሚኒስቴር የአርሶ አደሮችን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ በርካታ ሥራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል። ወደፊትም የግብርናውን ዘርፍ በማዘመን ምርታማነት ለማሳደግ ይሠራል። ከዓለም ባንክ የተገኘው ድጋፍ በሁሉም የግብርና ዘርፍ የሚሠራ ፕሮጀክት በመሆኑ የግብርናውን ዘርፍ ለማዘመን ጠቃሚ ነው። በመሆኑም በአዝርዕት፣ በእንስሳት፣ በተፈጥሮ ሀብትና በግብይት ላይ ሰፊ ሥራ ይሠራል ብለዋል።

የገንዘብ ድጋፉ የምግብ ሥርዓትን ለማጠናከር፣ ድህነትን ለመቀነስ፣ የሥራ ዕድል ለመፍጠር፣ የገበሬዎችን ምርታማነት ለማሳደግ፣ የመስኖ ሥራዎችን ለመስራት እና የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም እንደሚውል አስገንዝበዋል።

በዓለም ባንክ የኢትዮጵያ፣ የሱዳን፣ ደቡብ ሱዳንና ኤርትራ ዳይሬክተር ኡስማን ዲዮን በበኩላቸው፣ ዓለም ባንክ የኢትዮጵያ የምግብ ሥርዓት ፕሮግራም እንዲጠናከር ድጋፍ ማድረጉን ተናግረው ቀጣይነት እንዲኖረውም ይሠራል ብለዋል። የምግብ ሥርዓት ችግር የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካም ጭምር መሆኑን ጠቁመው፤ ችግሩን ለመቅረፍ በጋራ መሥራት ያስፈልጋል ሲሉ አሳስበዋል።

ኢትዮጵያ ያገኘችው የሥርዓተ ምግብ ማጠናከሪያ ፕሮግራም ትልቅ ዕድል ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፣ ፕሮግራሙ ውጤታማ እንዲሆንና በታሰበው ልክ እንዲሄድ ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ድጋፍ ጠይቀዋል።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ኢትዮጵያ ከፍተኛ ዕድገት እያስመዘገበች እንደሆነ የገለፁት ዳይሬክተሩ፤ አገሪቱ የአየር ንብረት ለውጥን እየታደገች በመሆኑ በቀላሉ የግብርና ዘርፉን ማዘመን እንደሚቻል አንስተዋል።

# 20 ኢንቨስተሮች በስኳር ኢንዱስትሪ ለመሰማራት ፍላጎት አሳይተዋል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**



አዲስ አበባ፡- 20 የአገር ውስጥ ባለሀብቶችና የውጭ አገር ኢንቨስተሮች ወደ ግል ሴክተር የሚዞሩ ስምንት የስኳር ፋብሪካዎችን በመግዛት በዘርፉ ላይ ለመሰማራት ፍላጎት ማሳየታቸውን የገንዘብ ሚኒስቴር አስታወቀ።

በሚኒስቴሩ የለውጥ ሥራዎች አማካሪ ወ/ት ሂንጃት ሻሚል ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በስኳር ኢንዱስትሪው ዘርፉ ለመሳተፍ ፍላጎት ያላቸው የግል ኢንቨስተሮች መሳተፍ እንደሚችሉ በተደረገው ጥሪ መሠረት ከ20 በላይ የሚሆኑ የግል ተቋማት መሳተፍ እንደሚፈልጉ ከወዲሁ አሳውቀዋል።

በስኳር ኢንዱስትሪው ዘርፍ የሚሰማሩ ኢንቨስተሮችን ፍላጎት ተከትሎ ሚኒስቴር መስሪያቤቱ ቡድን በማዋቀር የግል ተቋማቱ ያቀረቧቸውን የተለያዩ ጥያቄዎች ተመልክቷል ሲሉ አማካሪዋ ተናግረዋል።

ፋብሪካዎቹ ለአገር የሚያስገኙትን ትርፋማነት በተመለከተ እና ኢንቨስተሮቹ ያቀረቧቸው ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ ያስገባ የፕራይቬታይዜሽን ሂደቱን ያማከለ ምክረ-ሀሳብ እየተዘጋጀ መሆኑንም አመላክተዋል።

እንደ አማካሪዋ ገለጻ፤ ወደ ግል የሚዛወሩት የስኳር ፋብሪካዎች ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኙ፣ የማምረት አቅማቸው ምን ያህል እንደሆነ፣ ከማምረት ሂደት ጋር በተያያዘ መንግሥት ምን ዓይነት ፖሊሲ ሊያወጣ ይችላል፣ ሙሉ በሙሉ በግል ነው ወይስ በከፊል ሆኖ በሽርክና መሥራት አለባቸው የሚለውን ጉዳይ የያዘ ሰነድ እየተዘጋጀ ይገኛል።

በሚቀርበው ምክረ-ሀሳብ መሠረት መንግሥት ምላሽ ከሰጠበት በኋላ በሚቀጥሉት አምስት ሳምንታት ውስጥ የስኳር ፋብሪካዎቹን ወደ ግል ለማዞር የሚረዳ ጨረታ እንደሚወጣ አማካሪዋ አስታውቀዋል።

ፍላጎት ያሳዩ ኢንቨስተሮች ስለፋብሪካዎቹ ሁኔታ መረጃ እንዲያገኙ ተደርጓል ያሉት ወ/ት ሂንጃት፤ የተወሰኑት ኢንቨስተሮች ስኳር ፋብሪካዎቹ የሚገኙበት ቦታ ድረስ በመሄድ ጉብኝት ማድረጋቸውን ጠቁመዋል።

አማካሪዋ እንዳስታወቁት፤ የተመረጡት ስምንት ስኳር ፋብሪካዎች ወደ ግል ሴክተር እንዲዛወሩ መንግሥት ያቀደበት ዋነኛ ምክንያት ፋብሪካዎቹ አመርቂ ውጤት ማምጣት ስላልቻሉ እና የመሠረተ-ልማት ዝርጋታዎችን ሙሉ በሙሉ ስላላሟሉ ነው።

ፋብሪካዎቹ ወደ ግል አምራቾች ሲዛወሩ የተሻለ አቅም እንደሚፈጠርላቸውና ምርታማነታቸው እንደሚያድግ ይታመናል ብለዋል።

ፋብሪካዎቹ ተጨማሪ ኢንቨስትመንት ስለሚፈልጉ እንዲሁም በግሉ ዘርፍ የብዙ ጊዜ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች ቢሳተፉበት ውጤታማ ይሆናሉ የሚል ዕሳቤ እንዳለም አስረድተዋል።

የተመረጡት ስኳር ፋብሪካዎች ወደ ግሉ ዘርፍ ሲዞሩ በተለያዩ አገራት በዘርፉ ልምድና ካፒታልን ያካበቱ ኢንቨስተሮችም አብረው ይመጣሉ። ይህም በስኳር ኢንዱስትሪው ዘርፍ የካበተ ልምድ ካላቸው አገራት ዕውቀት፤ ክህሎትና ካፒታልን ለመጋራት ይረዳል ሲሉ ተናግረዋል።

የስኳር ፋብሪካዎቹ ወደ ግል የማዞር ሥራው በአገራችን አዳዲስ ካፒታል ለመሳብ በሚደረገው ጥረት ጉልህ ሚና እንደሚኖረው የጠቆሙት አማካሪዋ፤ ኢንቨስተሮቹ የካፒታል አቅማቸውን ተጠቅመው ምርታማነትን ሲያሳድጉ ኢትዮጵያ ስኳርን በብዛት ወደ ውጭ በመላክ የምንዛሬ አቅሟን እንድታሳድግ ዕድል ይፈጠራል ነው ያሉት።

ወደ ግል ሴክተር እንዲዞሩ የተለዩት ስኳር ፋብሪካዎች ኦሞ ኩራዝ 1፣2፣ 3፤ አርጆ ዴዴሳ፣ ከሰም፣ ተንዳሆ እና ጣና በለስ ፋብሪካዎች ወደ ግሉ ሴክተር ከሚዞሩት መካከል እንደሆኑ ተናግረዋል።

# «በከተማዋ በቂ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ቤት ተቀጥሬ መስራት ከጀመርኩ አምስት ዓመት አልፎኛል። ነገር ግን የጤፍ ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ በመጨመሩ ምክንያት ቤተሰቤን ለማስተዳደር እንደዚህ የተቸገርኩበት ወቅት የለም ብለዋል። ስለዚህ ይህ ጉዳይ ሥር ሳይሰድ የሚመለከታቸው የመንግሥት ተወካዮች ችግሩን በአስቸኳይ እንዲፈቱት ጥሪ አቅርበዋል።

ኅብረተሰቡ ለዕለት ፍጆታ የሚውሉ ምርቶችን በአቅራቢያው በተመጣጣኝ ዋጋ ሊያገኝ ይገባል፤ እየታየ ያለው የገበያ ዋጋ ግን የሚቀመስ አልሆነም። በተለይ ዝቅተኛ ገቢ ያለው ማኅበረሰብ የዋጋ ጭማሪውን መቋቋም አልቻለም ያለው ደግሞ የአዲስ አበባ ነዋሪ አቶ አብርሃም ዳኜ ነው።

የዋጋ ጭማሪ ለዕለት ተዕለት በሚውሉ ምርቶች ላይ መደረግ የለበትም። የአገር ውስጥ ምርቶች ላይ የሚደረገው የዋጋ ጭማሪ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ያሉ የማኅበረሰብ ክፍሎችን መሠረት ያደረገ አይደለም ሲልም ነው የሚገልጸው።

መንግሥት ለዕለት ተዕለት ፍጆታዎች የዋጋ ተመን አውጥቶ ሕግ የሚተላለፉ አካላት ላይ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ይጠበቅበታል ሲልም አሳስቧል።

በልደታ ክፍለ ከተማ የወፍጮ ቤት ባለቤት አቶ ሰለሞን ባይሳ (ስማቸው የተቀየረ) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የጤፍ አቅርቦት ችግር እና የዋጋ ጭማሪው ከኅብረተሰቡ ጋር ያለመተማመን ሁኔታ ውስጥ ከቶኛል። ወፍጮ ቤቴን ለአራት ቀን አልከፈትኩም። ለኅብረተሰቡ የምሸጠው ጤፍ ስለሌለ ኅብረተሰቡ ጤፍ የደበቅኩ እየመሰለው ነው።

ስለሆነም ከኅብረተሰቡ ጋር ላለመጋጨት ጥቂት ጤፍ ያላቸው ነጋዴዎችን ተለማምጬ ለኅብረተሰቡ ጤፍ አምጥቻለሁ። የኅብረተሰቡ አቅም እና የገበያው ሁኔታም የሚጣጣም አይደለም። ስለዚህ መንግሥት ጉዳዩን በትኩረት ሊያስብበት ይገባል ብለዋል።

የእህል በረንዳ ነጋዴ የሆኑት አቶ አማን ይሁን (ስማቸው የተቀየረ) በበኩላቸው፤ መንግሥት የንግድ ዘርፉን እንዲቆጣጠሩ ኃላፊነት የሰጣቸውን አካላት በዘርፉ ምን እየሠሩ እንደሆነ መመርመር ያለበት ሲሆን በኬላዎች አካባቢ እየተሠራ ያለውን ኢኮኖሚያዊ አሻጥር ከሥር ነቅሎ ማጥፋት አለበት ብለዋል።

ወቅቱ ከፍተኛ ምርት ያለበት እና ኢትዮጵያ ሰላም የሆነችበት ወቅት ነው። በዚህ ወቅት በተለየ ሁኔታ የእህል ዋጋ እንደ ሰማይ እየራቀ በመምጣቱ ዜጎችን ይበልጥ እያስጨነቀ ነው። ስለሆነም ይህንን ጉዳይ መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ መፍታት እንዳለበትም አቶ አማን አሳስበዋል።

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር ወ/ሮ በላይነሽ ረጋሳ በበኩላቸው፤ አጠቃላይ የኑሮ ውድነቱን በተመለከተ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እንደማይመለከተው እና ጉዳዩ ዘርፈ ብዙ ተዋንያን ያሉት ነው ብለዋል። ዋጋ ባልወጣበት ነገር ላይ ኃላፊነት መውሰድ እንደማይቻልም ገልጸዋል። ሚኒስቴር መስሪያቤቱ አሁን ለተፈጠረው የጤፍ ዋጋ ኃላፊነት «ማንዴት» የለውም የንግድ ሥርዓቱን በተመለከተ አጥንተን በቀጣይ ምላሽ የምንሰጥበት ይሆናል ብለዋል።

የጤፍ ዋጋ ግብይት ሥርዓቱን በተመለከተ የአዲስአበባ ከተማ ንግድ ቢሮ ምላሽ እንዲሰጠን ብንጠይቅም በከተማ አስተዳደሩ በኩል ግብረኃይል መቋቋሙን በመግለጽ የደረሰበትን በቀጣይ እናሳውቃለን ከማለት ውጪ ተጨማሪ አስተያየት ከመስጠት ተቆጥበዋል።

# በሶማሌ ክልል...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ጨምሮ ወደ 340 ሺህ የሚጠጉ እንስሳት በድርቁ ምክንያት የሞቱ ሲሆን ወደ 600ሺህ የሚጠጉት ደግሞ እጅግ አስጊ ሁኔታ ውስጥ ይገኛሉ።

ምንም እንኳ ችግሩ ሰፋ ያለ ቢሆንም በተለይ የመጠጥ ውሃ እንዲሁም ሌሎች ሰብዓዊ ርዳታዎችን የማቅረብ ሥራ በመንግሥትና በሌሎች ግብረሰናይ ድርጅቶች እየተሠራ መሆኑን የገለጹት አቶ አብዱልቃድር፤ ከሰሞኑ የብሔራዊ አደጋ ሥጋትና ሥራ አመራር ኮሚሽን ከተለያዩ ዓለም አቀፍ የእርዳታ ድርጅቶችና የመንግሥት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ጋር በድርቅ ክፉኛ የተጠቁትን የአፍዴር፣ ዳዋና ሸበሌ ዞኖችን ጎብኝተው ባስቀመጡት አቅጣጫ መሠረት የእንስሳት መኖ ጭምር እየቀረበ ቢሆንም ከችግሩ ስፋት አኳያ በቂ እንዳልሆነ ገልጸዋል።

ድርቁን ለመግታት ቀደም ሲል በጥር ወር አካባቢ መፍትሄ የማፈላለግ ሥራዎች መጀመራቸውን ያነሱትን የቢሮ ኃላፊው፤ የድርቁን የጉዳት መጠን የሚያጠናና ሪፖርት የሚያቀርብ ኮማንድ ፖስት በማቋቋም በየዞኖቹ ከማሰማራት በተጨማሪ ከዓለም ባንክ በተገኘው ድጋፍ በክልሉ መኖ እየተመረተ እንዲሁም እያከማቸ ቢሆንም ከችግሩ ስፋት ጋር ሁሉንም ዞኖች ለማዳረስ እንዳልተቻለ አብራርተዋል።

በተመሳሳይ መልኩ ሕዝቡን ለመታደግ በዓለም ምግብ ፕሮግራም በሴፍትኔት አማካይነት ድጋፍ እየተደረገ እንደሚገኝ የጠቆሙት አቶ አብዱልቃድር፤ አብዛኛው የክልሉ ሕዝብ የሴፍትኔት ተጠቃሚ በመሆኑ አደጋው የከፋ እንደሚሆን ተናግረዋል።

በመሆኑም መንግሥት እያደረገ ያለውን ድጋፍ አጠናክሮ እንዲቀጥልና ችግሩ በመንግሥት ድጋፍ ብቻ የሚፈታ ባለመሆኑ ዓለም አቀፍ እርዳታ ድርጅቶችና መላው ኢትዮጵያዊና ትውልደ ኢትዮጵያዊ ለክልሉ ድጋፉ እንዲያደርግ ጠይቀዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ድርቅን በዘላቂነት ለመቋቋም ለሚያስችሉ ተግባራት ትኩረት ይሰጥ!

የኢትዮጵያን ገናና ታሪክና የነጻነት ልዕልናዋን ከሚገዳደሩ ተግባራት አንዱ እና ቀዳሚው ድርቅ እና ድርቅን ተከትሎ የሚከሰቱ የረሃብ የታሪክ ገጿ ተጠቃሽ ነው፡፡ ይህ የቀደመ የታሪክ ገጿ ታዲያ "ኢትዮጵያ" የሚለውን ስም የቃላት መፍቻዎች ከረሃብ እና ድርቅ ጋር አያይዘው እንዲያስፍሩት ያደረገ ጭምርም ነበር፡፡

ምንም እንኳን ይሄንን ስም ለመቀየር በተወሰዱ ተግባራት የስሙን ትርጓሜ ከመዝገበ ቃላት ላይ እንዲፋቅ ማድረግ ቢቻልም፤ ኢትዮጵያን ግን እየደጋገመ ከሚጎበኛት አስከፊ ድርቅ፤ ዜጎቿንም አልፎ አልፎ ደግሞ ይሄን ተከትሎ ከሚከሰት ረሃብ ሙሉ በሙሉ መላቀቅ አልተቻለም፡፡ በዚህ ረገድ የሩቁ ቀርቶ ቀረብ ካሉት አንጻር እንኳን ሲታይ በንጉሱ፣ በደርግ፣ በኢህአዴግም ሆነ በብልጽግና የአስተዳደር ዘመናት በየአስር ዓመቱ፣ በየአምስት ዓመቱ፣ በየሁለት ዓመቱ እየተደጋገመ ከመከሰት አልፎ፤ በአንዳንድ አካባቢዎች አሁን ላይ ለተከታታይ አምስት የዝናብ ወቅቶች ሰማይ ለምድር ውሃ ለመለገስ የጨከነበትን ወቅት መመልከት ተችሏል፡፡

በኦሮሚያ ክልል ቦረናን ጨምሮ አስር በሚደርሱ ዞኖች የተከሰተው ድርቅ እና ይሄን ተከትሎ ዜጎች ለከፋ የሰብዓዊ ችግር የተዳረጉበትን እውነት፤ በሶማሌ፣ በደቡብ እና ሌሎችም አካባቢዎች መሰል ችግሮችን እየተጋፈጡ ያሉ ወገኖችን እንደ ማሳያ መጥቀሱም የችግሩን አሳሳቢነት ለመገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡ ለምሳሌ፣ በቦረና ዞን በተከሰተው ድርቅ ምክንያት የእንስሳት "ዝርያን ለማቆየት" በሚባል ደረጃ እስከ መግለጽ የደረሰ የከፋ ችግር ገጥሟል፡፡

በአካባቢው ነዋሪ የሆኑ ዜጎችም እንስሳቶቻቸውን ከማጣታቸውም በላይ ሕይወታቸውን ለማቆየት የሚችሉበትን እህል ውሃ ለማግኘት እጃቸውን ለመዘርጋት ተገድደዋል፡፡ የችግሩን አሳሳቢነት የተገነዘበው መንግስት እና መላው ሕዝብም ለወገኖቹ ለመድረስ የአስቸኳይ ሰብዓዊ ድጋፍ በማድረስ የወገኖቹን ሕይወት እየታደገ፤ ለእንስሳቱም መኖ እያቀረበ ይገኛል፡፡

ይሄን አይነት ድርቅ ሲከሰት ችግሩን በጊዜያዊነት ለመሻገር እና ዜጎችን ለመታደግ የሚሰሩ ስራዎች ይበል የሚያሰኙ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ለጊዜውም ቢሆን ዜጎች ሕይወታቸውን እንዳያጡና ችግሩን እንዲሻገሩ ያደረግልና፡፡ ይሁን እንጂ ድርቅ በመጣ እና ዜጎች ችግር ላይ በወደቁ ቁጥር የሚከወን የአስቸኳይ ድጋፍ ብቻውን የዜጎችን ሕይወት ሊለውጥ፤ ዘላቂ መፍትሄም ሊያመጣ አይችልም፡፡ በመሆኑም ድርቅ በተከሰተ ቁጥር ከሚከወን የሰብዓዊ ድጋፍ የዘመቻ ስራ የተሻገረ ተግባርን መከወን የተገባ ነው፡፡

በዚህ ረገድ አስቸኳይ የሰብዓዊ ድጋፍ ከማድረስ በተጓዳኝ፤ ተደጋጋሚ ድርቅ የሚያጠቃቸውን ቦታዎች እንዲሁም፣ በሰው ሰራሽ ችግር ምክንያት ለድርቅ እና ሌሎች ተፈጥሯዊ አደጋዎች የመጋለጥ ስጋት ያንዣበበባቸውን አካባቢዎች መለየት የመጀመሪያው ስራ ሊሆን ይገባል፡፡ እነዚህ ቦታዎች ከተለዩ በኋላ፣ እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ የየአካባቢውን ማኅበረሰብ ባሳተፈ እና ባለቤት ባደረገ መልኩ ድርቅን ለመከላከል የሚያስችሉ የተፋሰስ ልማት ሥራዎች፤ የአረንጓዴ አሻራ ስራውን የሚደግፉ የችግኝ መትከል ተግባር፤ የውሃ ማቆር እንዲሁም አነስተኛ እና መካከለኛ የመስኖ ልማት ስራዎችን ለማከናወን የሚያስችሉ ግድቦችን መገንባት ያስፈልጋል፡፡

ይሄን መሰል ተግባር በአንድ በኩል የአካባቢውን ለድርቅ የመጋለጥ ዕድል የሚቀንስ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ድርቅ ቢከሰት እንኳን ቀደም ብሎ የሚያዙ ውሃዎች እና የተሰሩ ግድቦችን ተጠቅሞ የመስኖ ስራዎችን ለማከናወን እና ችግሩን በራስ አቅም ለማሻገር የሚቻልበትን እድል ይፈጥራል፡፡

በዚህ ረገድ ቀደም ሲል ድርቅ በተደጋጋሚ በሚያጠቃቸው አካባቢዎች የተሰሩ የተፋሰስ ስራዎች ያመጡትን ውጤት ለዚህ እንደ አንድ የውጤታማነት ማሳያ ተሞክሮነት የሚወሰዱ ሲሆን፤ በአንጻሩ ለአምስት ተከታታይ የዝናብ ወቅቶች ዝናብ ርቆት ለከፋ ድርቅ የተጋለጠው የቦረና ዞን ከእለት የተሻገረ ሩቅ አስቦ ያለመስራት የሚፈጥረውን ችግር ሕያው ምስክር ሆነው ይገለጻሉ፡፡ በመሆኑም ድርቅን ተከትለው የሚከሰቱ ችግሮችን ለመከላከል ከዕለት ደራሽ ድጋፍ ያለፈ ድርቅን በዘላቂነት ለመቋቋም ወደሚያስችሉ ተግባራት ተገቢም የግድም ነው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን
**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የኢትዮጵያውያን ህያው ቅርስ -ዓድዋ

ራስወርቅ ሙሉጌታ

የጥቁር ሕዝቦች ምድር ያፈራቸው የምድረ ቀደምቷ ኢትዮጵያ ልጆች «እንደ አንድ ልብ መካሪ፤ እንደ አንድ አንደበት ተናጋሪ» ሆነው ዘመን የማይሽረው ታሪክ ከሰሩ ይኸው ዘንድሮ መቶ ሃያ ሰባት ዓመት ሞላቸው - ዓድዋ። ዓድዋ በስሙ የጥቁር ሕዝቦች ድል ይባል እንጂ የተሰራው ስራ የተጀገነው ጀግንነት የተገኘው ውጤት በጥቅሉ በተገዢነት ቀንበር ውስጥ ለነበሩት ሁሉ የድል ብስራትን ያበሰረ ነው። በርካታ ሕዝቦች ለአንድ አላማ የተሰለፉበትና አኩሪ ገድል ያስመዘገቡበት የታሪክ ክስተትም ነው።

ድሉ የጥቁር ሕዝቦችን አንገት ቀና ያደረገ ፤ የስልጣኔ ማማ ላይ ተቀምጠናል ያሉትን ደግሞ የሰው አምሳል ይሉት ስለነበረው የጥቁር ሕዝብ ደግመው ደጋግመው እንዲያስቡ ያደረገም ነበር። ይህ በቃላት ለመግለጽ የሚያዳግት ብስራት ከተከወነ ምእተ አመት ቢያልፈውም የድሉ ትኩሳት ዛሬም በልብ ውስጥ ስሜት ይፈጥራል። ዘመን የማይሽረው የዓድዋ ድል በትውልድ ቅብብሎሽ እየተወሳ እንደ አዲስ መጽሐፍ እየተገለጠ ብዙዎችን እያስተማረ ዛሬ ላይ ደርሷል።

የዓድዋ ድል የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ቅድም አያቶች የተጋድሎ ውጤት ብቻ ሳይሆን ዛሬም ድረስ የሚያወሳው የማይዳሰስ ቅርሱ ነው። የዓድዋ ድል ዛሬ ላለው ከመቶ ሚሊየን በላይ ለሚገመት ኢትዮጵያዊ ትምህርት ቤቱም ቤተ መጻሐፍቱም ነው። ለዚያውም የህብረትን የአንድነትን ምንነት የሚገነዘብበት፤ ነጻነት የሚለውን ቃል አፉን ሞልቶ የሚተረጉምበት የጀግኖች አባቶቹ ዘመን የማመይሽረው ውድም ክቡርም ስጦታ።

እንደ ዛሬው የህዳሴ ግድብ ሁሉ የዓድዋ ድል ላይ አሻራ የሌለው ደሙ ያልፈሰሰ አጥንቱ ያልተከሰከሰ የኢትዮጵያ ሕዝብ የለም። በዘመኑ የነበረውን ሕዝብ ያሰባሰበውም የነጋሪቱ መጎሰም የአዋጁ መነገር ብቻ ሳይሆን በእያንዳንዱ ልብ የነበረው የሀገርና የሕዝብ ፍቅር፤ የባርነትና የተገዢነት ጥላቻ ነበር። ይህ ነበር የቀጠሮ ቦታና ጊዜ ሳያዛንፍ በጎርፍ የሚመስል ሕዝብ በአንድ የተከሰተው - ለአደራ እናቱ ለኢትዮጵያ። ይህ ጀግና ሕዝብ ያኔ ነበር ከዘመናት በፊት እያንዳንዱ ሰው ተወልዶ የሚኖርበት የሚሞትበት የሚሞትለት ሀገር ሊኖረው እንደሚገባ የተረዳው።

ኢትዮጵያ ባህር አቋርጦ ስምና ክብሯን ገፎ ልጆቿን ከፋፍሎ በቅኝ ግዛት ቀንበር ስር ሊያውል ለመጣው ጠላቷ ተገቢውን ምላሽ የሰጠችው በሁሉም ልጆቿ ተሳትፎም ነበር። የክተት አዋጁ ከተነገረበት ቅጽበት አንስቶ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ልብ ወደዓድዋ መዝመት ጀምሮም ነበር። የሚዘምተው ጥይትና ዝናሩን አቅሙ የፈቀደውም ለጭነት ይሆን ዘንድ ፈረስ፤ በቅሎና አህያውን ሲያዘጋጅ ነበር። እናቶችና ሚስቶችም የጣይቱ ብጡልን አርአያነት በመከተል ከስንቅ ዝግጅት ከወንድ እኩል ወደ ጦር ግንባር እስከ መዝመት የሚጠበቅባቸውን ሳይሆን ከሚጠበቅባቸው በላይ ከፍለዋል። አገር ከሌለች ምንም እንደማይኖር ሃይማኖትም አደጋ ላይ እንደምትወድቅ የተረዱ የሃይማኖት አባቶችም ለክተት አዋጁ ያላቸውን ህብረት የገለጹት ውለው ሳያድሩ ነበር።

የኪነ ጥበብ ሰዎችም የነበራቸው አብርክቶ ከድሉ ዋዜማ የጀመረ ነበር። እንኳን በዛ ዘመን ዛሬም ኢትዮጵያ ጠርታው ጆሮ ዳባ ልበስ የሚል ባይኖርም ሁሉም ሞቶ ሀገር ለማዳን መነሳት እንዳለበት ያዜሙት ሁሉ ሰርቶላቸው በልበ ሙሉነት ለማዋጋት በቅተዋል። የአዝማሪዎች ተሳትፎ ግን በዚህ ያበቃም አልነበረም ተአምር የተሰኘው ድል ከተገኘም በኋላ ታሪክ እየተወሳ እንዲኖር ብዙ ሰርተዋል።

እኛ የዚህ ትንግርት ጀግና የሆነ ሕዝብ ልጆች ነን። ዛሬ ወንድሞቻችንን አፍሪካውያን በየአመቱ የሚያከብሯቸው ብሔራዊ ቀናት የሚባሉት ከባርነት ቀንበር ከዘመናት ግዞት ነጻ የወጡበትን ነው። እነሱ ለዘመናት ያሳለፉትን የስጋና የህሊና ባርነት በሚገባ ስለሚገነዘቡት የነጻነት ቀናቸውን የሚያከብሩት በፍጹም ደስታ በአዲስ የሕይወት ምእራፍ ነው።

በየአደባባዮቻቸው የሚያዩዋቸው ነገሮች ሁሉ ከትላንት ማንነታቸውና ምንነታቸው ጋር የሰቀቀን ጥምረትን ያዘሉ ናቸው። እነዚህ ወንድሞቻችን በኢትዮጵያውያን ጀግኖች የተፈጸመው ገድል ምን ያህል እንደሚያስደስታቸው አይተናል። የድሉ ቀጥታ ተሳታፊ እነሱ ቢሆኑ ደግሞ ምን እንደሚሰማቸው መገመቱ የሚከብድ አይመስለኝም። ለዚህ ነው በርእሴ ዓድዋን ድል የመላው ኢትዮጵያውያን የማይዳሰስ ቅርስ ለማለት የወደድኩት።

እንግዲህ ከዚህ በኋላ ሊነሳ የሚገባው ጥያቄ ዛሬስ እኛ ከዓድዋ ምን እንማር ? የዓድዋ ድልስ ምን አስተማረን ? የዓድዋ ድልንስ ከዓመት ክብር በዘለለ ረቂቅ ሀብትነቱን፤ እሴትነቱን ተጠቅመንበታል ወይ የሚለው ይመስለኛል። አያቶቻችን የሰሩትን አኩሪ ተጋድሎ እንዳንረሳ አባቶቻችን በየአመቱ እያዘከሩልን ዛሬ ላይ ደርሰናል። የዚህ ታላቅ የነጻነት ጎህ ማሳያ ሕዝባዊ ክብረ በዓል መከበር ያለው ፋይዳ ሁሉም የሚገነዘበው ነው።

ከዚህ ባሻገር ሀገራችንም ሕዝባችንም ከዓመት ዓመት የሚፈልገው የዓድዋ አይነት ተጋድሎዎችን የሚፈልጉ በርካታ ጥያቄዎች አሉበት። ችግሮቹ ደግሞ ጀግና ሆነን... ጀግና ፈጥረን.... ከዓመት እስከ ዓመት እየሰራን ካልተሻገርናቸው ብዙ የሚያስከፍሉን ብሎም ከቅኝ ግዛት ዘመን ባልተናነሰ የሚያዋርዱንና ከሰውነት የውሃ ልክ የሚያወርዱን ናቸው።

የዓድዋ ድል በህብረት ከቆምን በአንድ ከመከርን የማንሻገረው ገደል አለመኖሩን የራሳችን ታሪክ ሆኖ የሚያስተምረን ነው። ሁሉም ሊባል በሚችል ደረጃ ዛሬ የተጋረጡብን ችግሮችም ደግሞ ህብረታችን ከጠነከረ ሳንነካቸው ሳንገፋቸው በነው የሚጠፉ ናቸው።

ለዚህ ከትናንቱ የዓድዋ ድላችን አብዝተን ልንማርበትና ከዛሬው ስህተታችን ልንታረም ይገባል። እለቱንም ስናስብ በዓመት አንድ ቀን አክብረንው ዓመት ሙሉ የምንኖረው የምንሆነው ብሎም በልቦናችን የሚቀመጥ የማይዳሰስ ቅርሳችን ሊሆን ይገባል የእለቱ መልእክቴ ነው።

> **ኢ**ትዮጵያ ባህር አቋርጦ ስምና ክብሯን ገፎ ልጆቿን ከፋፍሎ በቅኝ ግዛት ቀንበር ስር ሲያውል ለመጣው ጠላቷ ተገቢውን ምላሽ የሰጠችው በሁሉም ልጆቿ ተሳትፎም ነበር። የክተት አዋጁ ከተነገረበት ቅጽበት አንስቶ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ልብ ወደዓድዋ መዝመት ጀምሮም ነበር። የሚዘምተው ጥይትና ዝናሩን አቅሙ የፈቀደውም ለጭነት ይሆን ዘንድ ፈረስ፤ በቅሉና አህያውን ሲያዘጋጅ ነበር። እናቶችና ሚስቶችም የጣይቱ ብጡልን አርአያነት በመከተል ከስንቅ ዝግጅት ከወንድ እኩል ወደ ጦር ግንባር እስከ መዝመት የሚጠበቅባቸውን ሳይሆን ከሚጠበቅባቸው በላይ ከፍለዋል። አገር ከሌለች ምንም እንደማይኖር ሃይማኖትም አደጋ ላይ እንደምትወድቅ የተረዱ የሃይማኖት አባቶችም ለክተት አዋጁ ያላቸውን ህብረት የገለጹት ውለው ሳያድሩ ነበር

# ነፃ ሃሳብ

# ዓድዋ... የኢትዮጵያዊነት ደማቅ ታሪክ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

የካቲት 23 1888 የዛሬ መቶ ሃያ ሰባት ዓመት በኢትዮጵያ የታሪክ ድርሳን ላይ አንድ ታሪክ ተመዘገበ..ዓድዋ የሚል የስሞች ሁሉ፣ የክብሮች ሁሉ፣ የነጻነቶች ሁሉ በኩር። ሁለት በታሪክ፣ በባህል፣ በስልጣኔ፣ በአይዶሎጂ የተራራቁ ሀገራት/ ኢትዮጵያና ጣሊያን አንዱ በራስ ወዳድነት አንዱ ደግሞ በነጻነት ስም ጽንፍ ቆሙ። ከመዲናችን አዲስ አበባ በስተ ሰሜን አቅጣጫ በ1065 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የኢትዮጵያውያን የከፍታ ምኩራብ ዓድዋ ለህልውናቸው በተጉና በእብሪት በታጠቁ ሁለት ተቃራኒ ነፍሶች ተፋጠጡ።

እውነት፣ ጽናትና፣ አንድነት ህብረት ፈጥረው፣ ጀግንነት፣ አትንኩኝ ባይነትና የሀገር ፍቅር ስሜት አብረው ራስ ወዳዱንና እብሪተኛውን የፋሺስት ወራሪ ሀይል ለህልውናቸው የቆሙ ጥቁር ነፍሶች አሸነፉት። በዚህ የጥቁርነት ተጋድሎ ውስጥ እኔና እናንተ ተፈጠርን። በዚህ የአንድነት መንፈስ ውስጥ ጥቁርነት ለመለመ። አፍሪካ ቀና አለች። በነዚያ ስለክብራቸው ሞትን በደፈሩ፣ ስለ ነጻነታቸው መከራን በናቁ ኢትዮጵያውያን ተጋድሎ ዛሬን አየን።

በዓድዋ ማግስት ብዙ ነገር ተቀየረ።ዓለም አይታው የማታውቀውን የጀግንነት ወኔ ከወደ አፍሪካ በኩል አየች። ይህ የኢትዮጵያ የአንድነት መንፈስ በመላው አፍሪካ ተቀጣጥሎ አፍሪካን ነጻ አወጣ።ዓለም ደግሞ የተዛባውን የነጮች የበላይነት አስተሳሰብ እንድታስተካክል ተገደደች።ዛሬም ድረስ አፍሪካና ዓለም የዓድዋን ፍሬ እየበሉ ነው።ዛሬም ድረስ በመላው ዓለም የሚኖሩ ጥቁሮች ቀና ያደረጋቸውን ዓድዋን ያከብራሉ።ዓድዋ የእኔና የእናንተን ታሪክ የቀየረ የአባቶቻችን የተጋድሎ ውጤት ነው።ይህ ስም ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ዘላለማዊ ክብር፣ ለነጮቹ ደግሞ ዘላለማዊ ውርደት ሆኖ ዛሬም ድረስ ይወሳል፡፡

ከዓድዋ ድል ቀደም ብሎ በ1880ዎቹ አካባቢ ላይ በጀርመን በርሊን አውሮፓውያን አንድ ስብሰባ ተቀምጠው ነበር። የስብሰባው አላማ አፍሪካን በመቀራመት አንጡራ ሀብቷን የመመዝበር ምክክር ነበር። በዚህ የቀኝ ግዛት ምክክር ላይ አፍሪካውያንን ያዋረዱና ክብር የነኩ በርካታ ሀሳቦች ሲነሸራሸሩ ነበር።ጥቁርነት ባርነት ነው፣ ነጭ የኃይል፣ ጥቁርነት ደግሞ የደካማነት ምልክት እንደሆነ በሰፊው ሲወራ ነበር። በቅኝ ግዛት ስም በአፍሪካ አህጉር ላይ የበላይነታቸውን በማሳየት እንደፈለጉ ለመሆን የሚመጻደቁ ሀገራት ጥቂት የሚባሉ አልነበሩም።

እንዳሉትም ሰራዊታቸውንና የጦር መሳሪያ ቸውን ተማምነው አይረባም ወዳሉት አፍሪካ ዘመቱ። በጊዜው ኢትዮጵያን እንድትወር እድል ያገኘችው ሀገር ጣሊያን ነበረች።ጣሊያኖች በጀነራል አልቤርቶኒና በጦር አዛዣቸው ጄነራል ባራቴሪ እየተመሩ ኢትዮጵያ ደረሱ..ግን እንዳሰቡት የሆነ አንድም ነገር አልነበረም።በዓለም ታሪክ ታይቶም ተሰምቶም በማይታወቅ ሁኔታ ኢትዮጵያ ሀገራችን በባህላዊ የጦር መሳሪያ እየተመራች ዘመናዊውን የጣሊያን ወታደር ድባቅ መታችው፡፡

በመቶ ሺ የሚቆጠር የኢትዮጵያ ገበሬ ሰራዊት ከአንድ ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በጦር ሰራዊቱ አስፈሪ የሆነውንና በወታደራዊ አካዳሚ የሰለጠነውን የአውሮፓ ቅኝ ገዢ ሀይል ተቆጣጠረው። ዓለም ጉድ አለ...በአፍሪካ ሰማይ ስር የነጻነት ጮራ ፈነጠቀች።መላው የጥቁር ሕዝብ የባርነት ቀንበሩን ሰበረ።ይሄ ታሪክ ህብረት የወለደው የእኔና የእናንተ ታሪክ ነው።

ይሄ ታሪክ ጥቁርነትን ያገነነ የአባቶቻችን የሀገር ፍቅር ስሜት ነው።በዚህ ታሪክ ውስጥ ብሔርና ጎጠኝነት፣ እኔነትና ራስ ወዳድነት አልነበሩም።በዚህ ታሪክ ውስጥ ዘርና ቀለም፣ የአንተና የኔ አልነበሩም።ወንድማማችነት ያበበበት፣ ኢትዮጵያዊነት የጎመራበት ነበር።ፍቅር በተግባር ሲገለጽ ዓድዋን ይመስላል።አንድነትና ህብረት ሚዛን ላይ ሲያርፉ ኢትዮጵያዊነትን ይመዝናሉ። አባቶቻችን ይቺን ሀገር ሲተውልን በብዙ መስዋዕት ውስጥ አልፈው ነው...

ዓድዋ በሀገራቸው ቀልድ በማያውቁ ኢትዮጵያዊ አርበኞች ሞትና እንግልት የመጣ የጥቁሮች ድል ነው። ይህ ድል በአውሮፓ ቅኝ ግዛት ስር ላሉ አፍሪካውያን መታደስን ፈጥሯል።በባርነት ቀንበር ለተያዙ፣ ፍትህና እኩልነት ለተነፈጋቸው ጭቁን ነፍሶች ድህነት ሆኗል።ይሄ ብቻ አይደለም ታላቁ የዓድዋ ድል የዓለምን የፖለቲካ መልክና ርዕዮተ ዓለም ከቀየሩ ኩነቶች ውስጥ አንዱም ሆኖ አልፏል፡፡

የእንግሊዝ ጋዜጦች በፊት ገጻቸው ላይ በአፍሪካ ድል ማግስት የመጣውን አፍሪካዊ ማዕበል በመመልከት ‹የዓለም ታሪክ ተገለበጠ፣ ታላቅ የትውልድ ማዕበል በአፍሪካ ተቀሰቀሰ› ሲሉ ጽፈዋል። በኢንሳይክሎፒዲያ ብርታኒካ የነጻነት ተጋድሎ መሪዎች ጉባኤ ላይ የዘማናዊቷ ኢትዮጵያ አባት እየተባሉ የሚጠሩት ዳግማዊ አፄ ምኒልክ በሌሉበት የአፍሪካና የመላው ጥቁር ሕዝቦች የነጻነት ተጋድሎ መሪ ሲል መርጧቸዋል፡፡

ከዓድዋ የድል ዜና በኋላ በአፍሪካ ምድር በርካታ ተአምራቶች ተፈጥረዋል።የዓድዋ የድል ብስራት ለእኛ ለአፍሪካውያን የክብር ጮራን ሲፈነጥቅ ለነጮቹ ደግሞ የውርደት ማቅን አከናንቧል።ብታምኑም ባታምኑም የዓለም የኃይል ሚዛን የተዛባው ከዓድዋ ድል ማግስት አንስቶ ነው።የነጮች የበላይነት፣ የምዕራባውያን ፈታውራሪነት እክል የገጠመው ነጭ በጥቁር የተሸነፈ ማግስት ነው።

ዓድዋ ስም ብቻ አይደለም፣ ዓድዋ ተራራ ብቻ አይደለም...ዓድዋ ታሪክ ነው..ዓድዋ የጭቁን ሕዝቦች የነጻነት ነጸብራቅ ነው። በዚህ ስም ውስጥ የተፈጠሩ በርካታ ሀገሮች አሉ። ከዚህ ታሪክ ቀጥለው ሀገር የሆኑ በርካታ ጭቁን ሀገሮች አሉ።ይሄን ታሪክ ተደግፈው የቆሙ፣ ከወደቁበት የተነሱ በርካታ ሕዝቦች በዓለም ዙሪያ አሉ፡፡

ከጣሊያን ሽንፈት በኋላ ጣሊያን እንደነበረች አልቀጠለችም። ጣሊያን ብቻ አይደለችም አፍሪካና ዓለምም እንደነበሩ አልቀጠሉም። በፖለቲካቸው ላይ፣ በአስተሳሰባቸው ላይ ለውጥ አምጥተዋል። ዛሬም ድረስ ነጮች ያልመለሱት አንድ ጥያቄ ቢኖር የዓድዋን የድል ሚስጢር ነው። ዓድዋ ለነጮች ሁሌም ውርደት ሁሌም ጥያቄ ነው።አንዳንዶች ኢትዮጵያውያን አፍሪካውያን አይደሉም ሲሉ ለሽንፈታቸው ማስተባበያ ያቀርባሉ።

የተቀሩት ደግሞ ኢትዮጵያውያንን እንደ መለኮታዊ ሀይል ቆጥረው ለሽንፈታቸው የእምነ ታቸውን ኃይል ተጠያቂ ሲያደርጉ ይደመጣል። ኢትዮጵያዊነትን እንደ ሚስጢር ቆጥረው ዛሬም ድረስ ከነጥያቄያቸው የተቀመጡ ሀገራት ጥቂቶች አይደሉም።እውነት ነው ኢትዮጵያዊነት በአንድነት ሲታጀብ ሚስጢር ነው።ዓድዋ ለነጮቹ ጥያቄ.. ለእኛ ግን መልስ ነው፡፡

ከዓድዋ ድል በኋላ በጣሊያን ምድር ብዙ ነገር ሆኗል። የወቅቱ የጣሊያን ንጉስ አማኑኤል ኡምቤርቶ የልደት ቀን በመላ ሀገሪቱ የሀዘን ቀን እንዲሆን ተወስኗል። ዋና ከተማዋን ሮምን ጨምሮ ፍሎሬንስ፣ ሚላንና ቬነስ የመሳሰሉ ከተሞች ምኒልክ ለዘላለም ይኑር› በሚሉ ቁጣ በወለዳቸው ሕዝባዊ መፈክሮች ተጥለቅልቀው እንደነበሩ ታሪክ ይነግረናል። እዛም እዚም በነጮች መሸነፍ የተንገበገቡ እፍረት ወለድ የምዕራባውያንና የአውሮፓውያን የዝምታ ጉርምርምታ ሲደመጥ ነበር። ይሄ ሁሉ የሆነው በአንድነት በመቆማችን ነው።

የሀገር ጉዳይ ሁሌም ከፊት ነው...ሀገር ጉዳይ ከግለሰብ ጉዳይ በልጦ አያውቅም።በወቅቱ በአባቶቻችን መሀከላቸው ቅራኔ ነበር ግን በሀገር ጉዳይ ላይ በአንድነት ቆመው ዓድዋን ፈጠሩልን። እኛም ዛሬ ልዩነታችንን ወደ ጎን ብለን ሀገር መፍጠር ይኖርብናል። ልጆቻችን የሚኮሩበትን፣ መጪው ትውልድ የሚደነቅበትን የአባቶቻችንን አይነት ዓድዋ መፍጠር ግድ ይለናል። በፊታችን የእኛን አንድነት የሚሹ በርካታ ሀገራዊና ቀጣናዊ ጎዳዮች አሉ።

በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚው፣ በማህበራዊ ሕይወታችን ለራሳችንም ሆነ ለትውልድ ልንሰራው የሚገባ ዓድዋ አለ።ሕይወት እዛም እዚም መርገጥ አይደለም..ሕይወት እጅግ አስፈላጊ ነገሮችን ቅድሚያ በመስጠት መከወን ነው። የዓድዋ ድል የታላቅ አስተሳሰብ ነጸብራቅ ነው። የዓድዋ ድል የድንቅ ጥበብ፣ የድንቅ አስተውሎት ውጤት ነው። አባቶቻችን በበረታ ሀሳብ ቅድሚያ ለሀገር ሰጥተው ባይዋጉ ኖሮ ዓድዋን ለመፍጠር በቸገራቸው ነበር፡፡

ዛሬ ላይ እኔና እናንተ በግልም ሆነ በማህበራዊ ሕይወታችን እየባከንን ያለነው ቅድሚያ ለሚሰጠው ቅድሚያ ባለመስጠታችን ነው።ሀገራቸውን ከፊት ያደረጉ ሕዝቦች ሁሌም አሸናፊዎች ናቸው። የለያዩንን ነገሮች ወደ ጎን ብለን ወደ ትልቅ ሀገራዊ የቤት ስራችን እናማትር። የአባቶቻችን የማሸነፍ ጥበብ ለሀገራቸው ቅድሚያ መስጠታቸው እን ደነበር መቼም ልንረሳው አይገባም።እኔና እናንተም ለማሸነፍ ለሀገራችን ቅድሚያ መስጠት አለብን።

ከዓድዋ መማር አለብን፣ ከአባቶቻችን መማር አለብን..እንደ ዜጋ፣ እንደ መንግስት፣ እንደ ተፎካካሪ ፓርቲ ዓድዋና አርበኞቻችን የሚያስተምሩን ብዙ ነገሮች አሉ። ዓድዋ የሕብረ ብሔራዊነት፣ የአትንኩኝ ባይነት መንፈስ ነው። ለሀገርና ሕዝብ ቅድሚያ የመስጠት ዋጋ ነው። የእምነት፣ የጽናት፣ የአልበገሬነት ንቅናቄ ነው። እንደ ሀገር ከታሪካችን የምንማረው ብዙ ነገር አለ...ዓመት በመጣ ቁጥር ማክበር ሳይሆን እኛ የዚህ ትውልድ አብራኮች በአባቶቻችን መንፈስ ውስጥ መውደቅ አለብን። እነሱን መምሰል ይጠበቅብናል..

ማየት ብንችል፣ ወደሚያግባባን መራመድ ብንችል እስከዛሬ ድረስ ሲያገፋፉን የነበሩ ነገሮች ሁሉ እዚህ ግባ የማይባሉ እንደሆኑ እንደርስባቸው ነበር። በዓድዋ ማግስት እንንቃ ..አባቶቻችን በዘመናዊ ጦርና፣ በዘመናዊ መሳሪያ ነቅቶና በቅቶ የመጣውን ጣሊያንን በንቃት የበለጡት ለሀገራቸው ቅድሚያ በመስጠት ነው። ለሀገር ቅድሚያ መስጠት መንቃት ነው።ከዛሬ አርቆ ነገን ማየት የዚህኛው ትውልድ የቤት ስራ ነው፡

ከዓድዋና ከአርበኞቻችን ሀገር የማቆየት ተጋድሎ እንማር።ለጥቁርነት ጌጥ ከሆነው፣ ነጮችን ካስጎነበሰው ኢትዮጵያዊ አንድነታችን እንማር። በዓድዋ ላይ ቆመን መለያየት አይታሰብም።ዓድዋ ቋጠሮ ነው..እኔን ካንተ አንተን ከሌላው የቋጠረ የኢትዮጵያዊነት ድርና ማግ ነው። ዓድዋ የኢትዮጵያውያን እጆች በአንድነት የሳሉት የጋራ ስዕላቸው ነው።እጆቻችን ለታሪክ ብርቅ አይደሉም፣ ክንዶቻችን ለድል ሩቅ አይደሉም... የአባቶቻችንን የአንድነት መንፈስ መውረስ ከቻልን የምንሻትን ሀገር መፍጠር እንችላለን እላለሁ፡፡

**ከዓድዋ መማር አለብን፣ ከአባቶቻችን መማር አለብን..እንደ ዜጋ፣ እንደ መንግስት፣ እንደ ተፎካካሪ ፓርቲ ዓድዋና አርበኞቻችን የሚያስተምሩንብዙ ነገሮች አሉ። ዓድዋ የሕብረ ብሔራዊነት፣ የአትንኩኝ ባይነት መንፈስ ነው። ለሀገርና ሕዝብ ቅድሚያ የመስጠት ዋጋ ነው። የእምነት፣ የጽናት፣ የአልበገሬነት ንቅናቄ ነው። እንደ ሀገር ከታሪካችን የምንማረው ብዙ ነገር አለ...ዓመት በመጣ ቁጥር ማክበር ሳይሆን እኛ የዚህ ትውልድ አብራኮች በአባቶቻችን መንፈስ ውስጥ መውደቅ አለብን። እነሱን መምሰል ይጠበቅብናል...**

# የከፋ ብሔረሰብ ባህላዊ የሠርግና ለቅሶ ሥነ-ሥርዓት

ማህሌት አብዱል



ኢትዮጵያ በርካታ ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝቦች ያለባት ሀገር ነች።ዘርፈ-ብዙ ባህላዊ እሴቶች፣ ወግ ልማዶች መገኛም ነች።ይህች መልከ ብዙ ህብረ-ብሔራዊት ሀገር ታዲያ ዛሬም ድረስ አንድነቷንና ህብረቷን ከነውብ ባህሎቿ ጠብቃ ማቆየት የቻለችው በእነዚህ ለዘመናት ትውልድን እየተሻገሩ በመጡት እሴቶች፣ ወጎችና ልማዶች ነው።በዛሬው «የሀገርኛ» አምዳችንም ተዝቀው ከማያልቁት ውብ ባህላዊ ስርዓቶች መካከል አንዱ የሆነውን የከፋ ብሔረሰብ ወግና ልማድ በጥቂቱ ልናስቃኛችሁ ወደድን።

የከፋ ሕዝብና አካባቢው በተለይ የሚታወቀው የሀገሪቱ የኢኮኖሚ ዋልታ በሆነው ቡና ነው። በዚህም ከፋዎች በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በዓለም ሕዝብ ዘንድ እውቅና አላቸው። ከዚህም ባሻገር ይህ ብሔረሰቡ በሀገሪቱ በጥንታዊ የመንግስት ምስረታ ይታወቃል። ይህ ደግሞ የላቀ ታሪክ ባለቤት ያደርጋቸዋል። ለኢትዮጵያውያን የጋራ ጉዞ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ያበረከቱም እንደሆኑ ያረጋግጥላቸዋል። ዛሬ የምናነሳው ግን አንዱን ክፍሉን ነው። ይህም የዚህ ብሔረሰብ እሴት ከሆኑት ስርዓቶች ውስጥ ባህላዊ የሠርግ እና ለቅሶ ሥርዓቶቹን ሲሆን፣ ተከተሉን።

## የከፋ ሕዝብ የሠርግ ሥነ ሥርዓት

አቶ በቀለ ወልደማሪያም የተባሉ ፀሐፊ በ1996 ዓ.ም «የከፋ ሕዝቦች እና መንግሥታት አጭር ታሪክ» በሚል ርዕስ ባሳተሙት መፅሐፋቸው ላይ እንዳሰፈሩት፣ የከፋ ሰው በደስታም ጊዜ ደስታውን ይካፈላል።ለምሳሌ ልጁን የሚድር ቤተሰብ እንደቅርበቱና ከዚህ በፊት ይኸው ቤተሰብ ለሌሎች ባደረገው የድጋፍ መጠን ገንዘብ እንዲሁም ለድግሱ የሚሆን የተዘጋጀ የምግብና የመጠጥ አቅርቦት ትብብር ይደረግለታል። በሐዘን ጊዜም እንዲሁ የሐዘን ዘፈን እንደሚዘፈን ሁሉ በሠርግ ጊዜም የሠርግ ልዩ ልዩ ዘፈኖች ይዘፈናሉ።

ለሠርግ ብቻ የሚዜም ዜማ ያለና በተወሰኑ የሠርጉ ሂደቶች ለምሳሌ፡- በሁለቱ ሙሽሮች ማለትም በወንድና ሴቷ ቤት ሲደርስና ሙሽሪትን ይዘው ወደ ወንዱ ቤት ሲደርሱ የተለያዩ ዘፈኖች ይዘፈናሉ።ይህ ደግሞ በህብረተሰቡ ዘንድ የተለመደ ነው።በተጨማሪም በዚህ የሠርግ አጋጣሚ ሌሎች የተለያዩ መልዕክቶች ያሏቸው ዘፈኖች ለሚፈለገው አካል ይደርሳሉ።ይህ የሠርግ አጋጣሚ ወንዶችና ሴቶች በአንድነት እንዲዘፍኑና እንዲጨፍሩም ያደርጋቸዋል።

እንደ አቶ በቀለ ማብራሪያ፣ በከፋ ባህል መሠረት የተደበቁ ምስጥሮች እና አሽሙሮች እንዲሁም የተቋውሞ ወይም የጀብዱ ተግባራትን የሚያወሱ መልዕክቶች ዘፈን በማውጣት ይተላለፋሉ።በተለይም ከፍተኛ የመከፋት ሁኔታ ሲኖር አልፎ አልፎ ተቃውሞውን በልቅሶው ዜማ የማስተላለፍ ልምድ አለ።ሆኖም በዋናነት ሠርግና ክብረ በዓላት የሕዝብን ስሜት ለማስተላለፍ ልዩ አጋጣሚዎች ናቸው።

የከፋ ባህላዊ የጋብቻ ሥርዓት ለአቅመ-አዳም ለደረሰ ልጅ በወላጆቹና በዘመድ ጥቆማ ከተመረጠች በኋላ እና ከተቻለም ወንዱ በሆነ መንገድ እንዲያያት ከተደረገ በኋላ የሚጀምር ነው።ምርጫውም በተለያየ መንገድ ስለ ሥነ- ምግባሯና ሙያዋ እንዲሁም ስለቤተሰቧ ሥነ-ምግባር ጥናት ከተደረገ በኋላ ይከናወናል።በእናትም ሆነ በሰባት በኩል ዝምድና ብቻ ሳይሆን የጎሳ አንድነት ያላቸው ቤተሰቦች በፍጹም ሊጋቡ አይችሉም።ይህም ማለት ከሴትና ወንድ ተጋቢዎች እናቶችና አባቶች መሀል በእናትም ሆነ በአባት በኩል ለምሳሌ፡- በሴቷ አራት አያቶች እና ከወንዱ አራት አያቶች መሀል በጎሳ ተመሳሳይ የሆነ ካለ ጋብቻው ይቀራል ሲሉ አቶ በቀለ ያስረዳሉ፡፡

እናት ወይም ቤተሰቡና አግቢው ከተስማሙ በኋላ ሽማግሌ በመላክ ልመና ይደረጋል።የሴቷ ቤተሰብ ለመልሱ ቀጠሮ ይሰጣል፣ የራሱን ጥናት አድርጎ መልሱን ያሳውቃል።መልሱ አሉታዊ ከሆነ በአብዛኛው በመልዕክተኛ አማካይነት ለወንዱ ቤተሰብ ይደርሳል። አዎንታዊ ከሆነ ግን ቀድሞውኑ የተላኩት ሽማግሌዎች ተመልሰው እንዲሰሙ ቀጠሮው ይጠበቃል።ለዚህም በተለያየ መንገድና በተለይም በእናቷ በኩል የሴቷ ስሜት የሚጣራ ሲሆን የወላጆች ወሳኝነት ግን ከፍተኛ ቦታ ይኖረዋል፡፡

ከዚያም በሁለቱም ተጋቢዎች ቤተሰብ ቤት ሠርግ የሚደገስ ሲሆን፣ ጋብቻው በተራራቀ አካባቢ በሚገኙ ቤተሰቦችም መሐል ስለሚሆን የጥሎሽ ስጦታው የሚከናወነው በሠርጉ ዕለት ይሆናል። ይህም ሙሽራውና አጀቢዎቹ ከመድረሳቸው አስቀድሞ የተወሰኑ ሰዎችን በመላክ የሚከወን ነው። የሚጠበቀውን ያህል ጌጣጌጥና ስጦታ ካልመጣ ግን ውዝግብ ሊፈጠር ይችላል። በአብዛኛው ግን በዋስ የሚያልቅበት ስርዓት አለ።ሆኖም ዋስ የተጠራበት ጉዳይ እስከ ምላሹ ዕለት ተሟልቶ መታየት ይኖርበታል።

እንደ ጸሐፊው ማብራሪያ፣ ወንዱ ሙሽራና አጃቢዎቹ ሲመጡ መቃረባቸውን የሚያሳውቁበት ልዩ መልዕክት አለ።ይኸውም «ሻሙቶ» የሚባል ከቀንድ የተሰራ የሙዚቃ መሳሪያ ድምጽ ነው። ከሙሽራውና አጃቢው ቀደም ብሎ በሚሄድ በሽማግሌዎች በሚመራ ቡድን የጥሎሽ አሰጣጡ ሥነ- ሥርዓት ይካሄዳል። ከዚያም ከሴቷ ቤተሰብ የይግቡ መልዕክት ሲደርስ የወንዱ አጃቢዎች ለሠርግ ብቻ የሚዘፈን ጨዋታ ይጀመራል። ወንዱን ሙሽራ የሚያሞግስና በትዳር ዘመናቸውም ከሴቷ የሚጠበቀውን ባህሪይ የሚያትት መልዕክት ያለበት ዘፈንም እየዘፈኑ ወደ ውስጥ ይዘልቃሉ።

በጋብቻው ወቅት ከወንዱ ወገን የቀኝ ሚዜና የግራ ሚዜ የሚባል ሁለት ሚዜዎች ይኖራሉ። ከሁለቱ ሚዜዎች የቀኝ ሚዜው ትልቅ ኃላፊነት ያለበት ነው። ምስጢረኛና የቁርጥ ቀን ጓደኛ ተደርጎ ይወሰዳል። በትዳር ዘመናቸውም በተጋቢዎች መሐል አለመግባባት ሲፈጠር የመጀመሪያው አማካሪና መፍትሔ ሰጪ እርሱ ነው። ይኸው የቀኝ ሚዜ በሠርጉም ዕለት ሙሽሪትን ከወላጆቿ ቤት ስትወጣ በጀርባው አዝሎ ከቤት የማስወጣት ኃላፊነት ያለበት ነው። በጉዞው ወቅትም ከዚሁ በተረፈ ለሙሽሪት ጃንጥላ መያዝ፣ በፈረስ ላይ ስትቀመጥ ከጎኗ ሆኖ ደግፎና ተንከባክቦ የማድረስ ኃላፊነት አለበት።ወደ ወንዱ ቤት ሲመለሱ በጉዞ ላይ ሙሽሪት ከፈረስ ላይ የምትወርድበት አጋጣሚ ቢፈጠር በእግሯ መሬት እንዳትረግጥ የመሸከም ወይም መርገጫ ማንጠፍም የቀኝ ሚዜ ግዴታ ነው ይላሉ ጸሐፊው።

በከፋ ባህላዊ ጋብቻ የሴት ሚዜ የሚባል ነገር የለም።በዕለቱም ሆነ በጊዜያዊነት ለተወሰነ ጊዜ ሴቷን የምትደግፍ ረዳት ሴት አብራ የምትሄድበት አጋጣሚ አይኖርም። ስለዚህም ተንከባካቢዋ የወንዱ ሚዜ ብቻ ነው። በጉዞ ወቅት ሙሽሮቹ በተለይም ሴቷ ሙሽራ የምትቀመጠው ፈረስ ወይም ባዝራ ላይ እንጂ በቅሎ ላይ አይደለም።ይህ የሚሆንበት ምክንያት ደግሞ በዋናነት በቅሎ መካን ስለሆነች ሙሽሪትም በቅሎ ላይ ከተቀመጠች መሐን ልትሆን ትችላለች ተብሎ ስለሚታመን ነው።በተመሳሳይ በቅሎ የመደንበር ባህርይ ሊኖራት ስለሚችል ከአደጋ ለመከላከል መሆኑን አቶ በቀለ ያስረዳሉ፡፡

በከፋ ባህል ሙሽሪት ስታገባ የተለያዩ ስጦታዎችን ከወላጆቿ ቤት ይዛ ትሄዳለች። ከእነዚህም ውስጥ በተለያየ ቀለማት ከተነከረና በትንንሹ ተሰንጥቆ ከተዘጋጀ ዘንባባ የሚሰራ ልዩ ውበት ያለው ‘ሻጎ’ የሚባል የሰሌን ምንጣፍ እና ትራስ አንዱ ነው። በተለያየ ሥዕል የተዋበና ከቆዳ የተሰራ ‘ናቶ’ የሚባል የመኝታ ምንጣፍና ትራስም ሌላኛው ነው። በሙሽሪት ቤት በሴቷ ወላጆችና ቤተሰብ እንዲሁም ወደ ሙሽራው ቤት ሲደርሱ በሙሽራው ወላጆችና ቤተሰብ አባላት የምርቃት ሥነ-ሥርዓት ይካሄዳል፡፡

ወንዱ ቤት ሲደርሱ ከሠርጉ ቤት ደጃፍ ‘አንብሮ’ የተባለ ነጭ ሰሌን ተነጥፎና ጦር ተተክሎ የሚጠብቃቸው ሲሆን፣ የቀኝ ሚዜው ደግፏት ሙሽሮቹና ሚዜዎች ጦሩን ሦስት ጊዜ ከዞሩ በኋላ ቁጢጥ እንዲሉ ተደርጎ ይመረቃሉ። ሙሽሮቹና ሚዜዎቻቸው ከተወሰኑ የቅርብ ጓደኞቻቸው ጋር በአብዛኛው ከወራት ወይም ከበርካታ ቀናት በኋላ ወደ ሴቷ ቤተሰቦች ለምላሽ የሚጠሩ ሲሆን በተለይም ሙሽሮቹ በምላሹ ወቅት ለቀናት በሴቷ ወላጆች ቤት ይቆያሉ።

ይህ የተለመደው የጋብቻ ሥርዓት ቢሆንም አልፎ አልፎ በጠለፋ ጋብቻ ሊፈፀም ይችላል።ይህም የሚሆነው ሽማግሌ ተልኮ የሴቷ ቤተሰብ ፍቃደኛነት ከተረጋገጠ በኋላ ለመሰረግ አቅም ሲያንስ ወይም አልመች ሲል፣ አልፎ አልፎም ሁለቱ ተጋቢዎች ከተፈቃቀዱና ከተስማሙ በኋላ የቤተሰብ ተፅዕኖ ሲኖር ሆኖ፣ በጣም በተወሰነ ደረጃ ግን ከሴቷ ወገንና ከቤተሰቦቿ አሉታዊ ምላሽ ተሰጥቶም ቢሆን በተወሰኑ ቤተዘመዶቿ በኩል ድጋፍ ሲኖር ሊሆን ይችላል።

በባህላዊ ሥርዓት ከዚህ ውጭና ምንም አይነት ፍንጭ ሳይሰጥ ጠለፋ አይካሄድም።ጠለፋ ከተካሄደም በኋላ ልጅቷ ስለመጠለፏና ማን እንደጠለፋት በተዘዋዋሪ መንገድ መልዕክት ለቤተሰቧ እንዲደርስ ይደረጋል። ቀጥሎም ከተወሰኑ ቀናት በኋላ ሽማግሌ ተልኮ ዕርቅ ይጠየቃል። በአብዛኛውም ከተደጋጋሚ ጥረት በኋላ ስምምነት ላይ ተደርሶ የሴቷ ቤተሰብ መልስ ይጠራል ሲሉ ነው አቶ በቀለ በመፅሐፋቸው ያብራሩት።

በከፋዎች ዘንድ ዝምድና አንዴ ከተመሰረተ ግንኙነቱ ጥብቅ ነው።ከዝምድና ሁሉ ደግሞ የአማችና ጋብቻ ወይም ‘ናቾ’ እና የሚዜነት ትስስር በከፍተኛ ክብርና ጥንቃቄ የሚያዝ ጠንካራ ግንኙነት ነው።በብሔረሰቡ የክርስትና ዝምድና (አበልጅነት) እና ሚዜነት ከሥጋ ዝምድና ያላነሰ ትስስርና ፍቅር ይቸረዋል።ለዚህ ግንኙነት የሚታጨው ሰውና ቤተሰብም ልዩ ክብር ያለው ከሆነ ነው።በጋብቻ ትስስር በተገናኙ ቤተሰቦችም መሀል መከባበር እንዳለ ሆኖ ከሁለቱም ወገን ታናናሾች ታላቆችን ከማክበራቸው የተነሳ ሰላምታ ሲሰጥ «መሬት ልተኛልዎ» (ሽዎች ቀቦና) በማለት እጅ የመንሳትና የማክበር ሰላምታ በመሰጣጣት ነው።በዚህ መልኩ ሰላምታ የቀረበለት ታላቅም የዚህን አፀፋ ከመሬት በላይ ኑር (ሾወ ዳምባ ቤብ) በማለት ይመልስለታል በማለት ያስቀምጡታል በመጸሐፋቸው።

## የከፋ ሕዝብ የለቅሶ ሥርዓት

አቶ በቀለ በመጽሐፋቸው እንዳስነበቡት፣ በከፋ ሰው ሲሞት የሃዘን ጥሪ ወይም የድረሱልኝ ጥሪ የሚተላለፈው ከእንጨት ተፈልፍሎ በተሰራ ገንዳ (ሆኮ) እንደ ደውል በመምታት ይሆናል።በጥሪው መሰረትም በመንደሩ ውስጥ የሚኖሩ ወንዶችና ሴቶች ይደርሳሉ። ሟች ያገባ ወይም ያገባች ከሆኑ የሩቅ ዘመድ አዝማድ እስከሚሰበሰብ ድረስ የቀብሩ ሥነ-ሥርዓት አይፈፀምም። እስከዚያው ድረስና ከቀብርም በኋላ በየለቅሶው ጣልቃ ወንዶችና ሴቶች ለየብቻቸው ክብ በመስራት በለቅሶ ጊዜ ብቻ ወይም ደግሞ አልፎ አልፎ በሕዝቡ ላይ በደል ሲደርስ መከፋቱን በተዘዋዋሪ መንገድ ለመግለፅ የሚያዘወትረውን ዜማና ልዩ ውዝዋዜ እያሰሙ ይቆያሉ።

ወንዶች ብቻ የሚሳተፉበት የለቅሶ ጊዜ ዜማና ውዝዋዜ ‘ሂቾ’ ሲባል፣ የሴቶች ደግሞ ‘ጎሞ’ በመባል ይጠራል። ይህም የዜማ ዓይነትና ውዝዋዜ በመሪርና፣ ሟችን የማያውቀውንም ጭምር በሚያስለቅስ የሙሾ ድርደራና ልቅሶ መሀል አልፎ አልፎ የሚካሄድ ነው።የሂቾና ጎሞ የግጥም ይዘት የሟችን ደግነት፣ ጀግንነት፣ ችሎታና ብቃት የሚዘረዝር ነው። እንዲሁም ስለሞቱና ከሞት በኋላ ስለሚታወስለት ደግ ሥራም ይወሳል።

ይህ ዜማና ውዝዋዜ በየለቅሶው መሐል ሲደረግ ለቀስተኛው መጠነኛ እረፍት እንዲያደርግና እንዲፅናና ይረዳል።ይሁንና ይህ ዜማና ውዝዋዜ ባለፉት ጊዜያት በተደረጉ የተለያዩ ተፅዕኖዎች የተነሳ እየተረሳና እየጠፋ የመጣ ቢሆንም በቅርቡ ደግሞ የተፈጠረውን አጋጣሚ በመጠቀም በብዙ አካባቢዎች እንደገና የማንሰራራት ሁኔታ ታይቶበታል ይላሉም ጸሐፊው።

በለቅሶ ጊዜ የሟች የቅርብ ዘመዶች ሁሉ ፀጉራቸውን ይላጫሉ፣ በአንገታቸው ላይ ነጭ ክር ያስራሉ የሚሉት ፀሐፊው፣ በጠቅላላው የሟች ቤተሰቦች መሪር ሐዘን የሚያዝኑበት ጊዜ ነው።ከቀብር በኋላም ለረጅም ጊዜ ከጎረቤትና ከዘመድ ቤት ቡና እና ቁርስ እንዲሁም ምግብና መጠጥ የሚቀርብ መሆኑን ይጠቅሳሉ። የዚህ አይነቱ እዝን ማምጣት ከጉርብትና እና ከዝምድና በተጨማሪ እንደ ብድርም ተደርጎ የሚወሰድ እንደሆነም ያስረዳሉ።

ጨና እና ጌሻ ወረዳ አካባቢ ደግሞ ከዋናው የለቅሶ ቀን ሌላ ቀጠሮ ተይዞ እና ከሩቅ ያለ ዘመድ ሁሉ ተነግሮት ደመቅ ያለ የለቅሶ ሥነ-ሥርዓት የሚካሄድበት ሁኔታ አለ። በተለይም በጋብቻ የተሳሰረ ማለትም አማች ከሆነ እንደዚህ ዓይነቱ ቀጠሮ ቀን በከፍተኛ አጀብ በመቅረብ ለቅሶና ሂቾ ማድረጋቸው ግድ እንደሆነ ያነሳሉ።

በከፍኛ ቋንቋ የመቃብር ቦታ ‘ማሾ’ የሚባል ሲሆን፣ በቀድሞው ዘመን ደግሞ የከፋ የመንፈስ አባቶች ወይም «አላሞ» እና ነገስታት የሚቀበሩበት ቦታ የተለየ እንደነበር የብሔረሰቡ ታሪክ ያስረዳል።ይህም የመንፈስ አባቶች የቀብር ቦታ ‘ጉቶ’ ሲባል የነገስታት ደግሞ ‘ሞጎ’ እያሉ ይጠሩታል። የነገስታቱን መቃብር በተመለከተ አቶ በቀለ በጽሁፋቸው ሲያስረዱ፣ ከመጨረሻው ንጉሥ ‘ከአዲዮ ጋኪ ሻሮቺ’ በስተቀር ሁሉም የከፋ ነገስታት የተቀበሩት በአንድ ቦታ ሲሆን፣ ይህም የነገስታት የመቃብር ቦታ የሚገኘው በጠሎ ወረዳ፣ ሻዳ ቀበሌ ልዩ ስሙ ሾሻ በሚባል አካባቢ ነው።የመንፈስ አባቶቹ ግን በየዝርያቸውና በሚወክሉት መንፈስ መሰረት ለየራሳቸው በተለዩ ቦታዎች ይቀበራሉ፡፡

ማህበራዊ

# ወጣቶች

## የአዲስ አበባ ወጣቶች ማህበር የ25 ዓመታት ጉዞ

**እፀገነት አክሊሉ**

25 ዓመት የአንድ ወጣት እድሜ ነው። አዎ እዚህ ለመድረስ ብዙ ዓመታትን ማለፍ ይጠይቃል። በእነዚህ ዓመታት ደግሞ ውጣ ውረዶችን ማየት ብሎም በእድሜ ሂደቱ የሚያመጡትን በጎና መጥፎ ነገሮችን መጋፈጥም የሚጠይቅ ነው። በሌላ በኩልም 25 ዓመት የሞላው አንድ ወጣት በኖረባቸው ዓመታት ባከናወናቸው ባለፋቸው መንገዶች ብዛት የተነሳ የሚጠበቁበትም በርካታ ውጤቶች መኖራቸው ግልጽ ነው። ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ ማደግ መማር ማወቅ መስራት አንዳንዴም ቤተሰብ መስርቶ ማስተዳደር ሊኖሩ ይችላሉ። ይህንን ማሳካት የቻለ ደግሞ እድሜውን በአግባቡ የተጠቀመ ወጣት ይባላል።

ለዚህ ሀሳባችን መነሻ የሆነን የ25 ዓመት የስራ ጊዜውን እያከበረ ያለው የአዲስ አበባ ወጣቶች ማህበር ጉዞ ነው። ማህበሩ ከዛሬ 25 ዓመት በፊት ሲመሰረት መነሻው የወጣቶችን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ነው። በእነዚህ ዓመታት ወጣቶች በማህበራዊ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዘርፎች ላይ የነቃ ተሳትፎን እንዲያደርጉ ብሎም ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችሉ ስራዎችን ለመስራትም ያለመ ነበር ።

እኛም ይህ እቅዱ ምን ያህል ተሳክቷል? ስንል የማህበሩን ዋና ጸሀፊ ወጣት ይሁነኝ መሃመድ አነጋግረናል። ወጣቱ እንደሚለውም የአዲስ አበባ ወጣቶች ማህበር የምስረታውን 25ተኛ ዓመት በዓል በማክበር ላይ ይገኛል። ማህበሩ ለመመስረቱ ዋና አላማው ደግሞ የወጣቶችን ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን ከመንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር ተቀናጅቶ ለመፍታት ነው።

እንደ ወጣት ይሁነኝ ገለጻ ማህበሩ እነዚህን አላማዎቹንም በመላው ከተማዋ የሚገኙ ወጣቶች ተሰባስበው ይወክሉናል የእኛን ጥያቄ ሊያነሱ ይችላሉ ያሏቸውን ወጣቶች በነጻነት መርጠው በኢፌዴሪ በጎ አድራጎትና ማህበራት ኤጀንሲ ዘንድ አስመዝግበውና ፍቃድ አግኝተው ወደ ስራ ገብተዋል። ወደስራ ለመግባቱም ዋና አላማ አድርጎ የተነሳው የወጣቶችን ጥያቄዎች እንዲፈቱ ማድረግ ነበር።

እነዚህን እንቅስቃሴዎች ሲያደርግ በተለይም በወጣቶች ዘንድ ሊታይ የሚችል አበርክቶው ምንድን ነበር? ተብለው ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱም፤ ማህበሩ ከመመስረቱ በፊት በግለሰቦች አነሳሽነት ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ እየተባሉ ችግሮች እየተለዩ ይሰራ ነበር እንጂ በትክክል ተለይቶ በመንግስት ደረጃ የወጣቶችን ችግር የሚፈታ ምንም ዓይነት ተቋም አልነበረም፤ በመሆኑም ማህበሩ መቋቋሙ በአገር ደረጃ የወጣቶች ፖሊሲ እንዲረቀቅ የራሱን አበርክቶ ያደረገ ሲሆን ከዛ ባሻገርም ወጣቶችን የሚመለከት እንደ ወጣቶችና ስፖርት⍰ ባህልና ቱሪዝም የሚባሉ ተቋማት ወጣቶችን ማዕከል አድርገው እንዲመሰረቱም ያደረገ ስለመሆኑ ያብራራሉ።

ሌላው ወጣቶች ትርፍ ጊዜያቸውን በአልባሌ ቦታ እንዳያባክኑ በአንጻሩ ደግሞ አንድ ቦታ ላይ ቁጭ ብለው እውቀታቸውን ተሞክሮዎቻቸውን እየተለዋወጡ የሚውሉባቸው ቦታዎችን ለማዘጋጀት እቅድ በመያዝና የወጣቶችን ማዕከል ጎተራ አካባቢ በመገንባት ለወጣቶች አስረክቧል። በአሁኑ ወቅትም በመላው ከተማዋ ከ 116 ያላነሱ ማዕከላት ተገንብተው ለወጣቶች የተለያዩ አገልግሎቶችን በመስጠት ላይ ይገኛሉ።

ማህበሩ ወጣቶች በተለያዩ የሙያ ዘርፎች ሰልጥነው ነገር ግን ወደስራ ያልገቡበትና ስራ በማጣት ምክንያት ወደተለያዩ አላስፈላጊ ድርጊቶች ውስጥ ሊገቡ የነበረበትን ሁኔታ ከኮካ ኮላ ጋር በመቀናጀት ኪዎስኮች እንዲከፈቱላቸው በማድረግ ስልጠናዎችን እንዲያገኙ በማድረግ ተሞክሮ ከቀመረ በኋላ ጥቃቅንና አነስተኛ የሚባለው ተቋም እንዲቋቋም በማድረግ ወጣቶች ሼዶችን አግኝተው በሙያቸው ስራዎችን እንዲሰሩ በዛም እስከ ባለሀብትነት እንዲደርሱ በማስቻልም በኩል ሚናው ከፍ ያለ እንደነበር ይናገራል።

የአዲስ አበባ ወጣቶች ማህበር አገራዊ ጉዳዮች ላይም የነቃ ተሳትፎን ያደርጋል ያለው ወጣት ይሁነኝ ለምሳሌ በአክሱም ሀውልት አስመላሽ ኮሚቴ ላይ እንደ አንድ ተቋም አባል ሆኖ ሲንቀሳቀስ የነበረ ነው።

ወጣቶች እንደ አገር የሚመጡ ጥሩም ይሁኑ መጥፎ ነገሮች ተጋላጭ የመሆን እድላቸው ሰፊ መሆኑን የሚናገረው ወጣት ይሁነኝ ማህበሩም በተለይም በ1997 ዓ.ም በነበረው ችግር ምክንያት በወጣቶች ላይ ይደርሱ



ወጣት ይሁነኝ መሃመድ
የአዲስ አበባ ወጣቶች ማህበር ዋና ጸሀፊ

የነበሩ እስሮችን ባሉበት ቦታ በመሄድ በመመልከት መስተካከል ያለባቸው ጉዳዮችም እንዲታረሙ ለመንግስት በማመላከት በኩል የበኩሉን ስለመወጣቱ ይናገራል።

ወጣቶች በጤናውም ዘርፍ ላይ ትኩረት ማግኘት አለባቸው በማለትም ኤች አይ ቪ ኤድስ በወጣቱ ላይ የከፋ ጫናን እንዳያደርስ የመከላከያ መንገዶቹን ከማስተማር ጀምሮ እንደ ተስፋ ጎህ ያሉ በጉዳዩ ላይ የሚሰሩ ተቋማት ሲቋቋሙ በማገዝ የበኩሉን ተወጥቷል። በሌላ በኩልም የዛሬ ወጣቶች የነገ አረጋውያን የማይሆኑበት ምክንያት የለምና እንደ መቄዶንያ አይነት የአረጋውያን እንክብካቤ ማዕከላት ሲቋቋሙ ድጋፍ በማድረግ የበኩሉን ስለመወጣቱ አብራርቷል።

አሁን ላይ በመላው አገራችን ተስፋፍቶ የሚገኘው የበጎ ፍቃድ እንቅስቃሴ አጀማመሩ በዋናነት በማህበሩ ነበር ያለው ወጣት ይሁነኝ በ1995 ዓ.ም ሃሳቡ ሲጠነሰስ ማህበሩ በተለይም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች የሆኑ ወጣቶች በጋውን ተምረው ክረምት ለእረፍት ወደየመጡበት ሲሄዱ በበጎ ፍቃድ ታናናሾቻቸውን በእውቀት እንዲያግዙ የማድረግ ስራ በአዲስ አበባ ጀምሮ እስከ 2000 ዓ.ም የመሪነት ቦታውን ይዞ ቆይቷል። በነገራችን ላይ ወጣቶች በበጎ ፍቃድ እንዲሰሩ ሲደረግ የነበረው ይህ ብቻ አይደለም ይልቁንም በትራፊክ ማስተባበር⍰ በደም ልገሳ በኤች አይ ቪ ትምህርት በመስጠት የአረጋውያንን ቤት በማደስና በሌሎችም ላይ ተሳትፎን እንዲያደርጉ ከፍ ያለ ድጋፍ ሲያደርግ መቆየቱን ጠቅሷል።

ይህ የማህበሩ ጅምር ደግሞ አሁን ላይ በመላ አገሪቱ ተስፋፍቶ ብዙ ባለቤት አግኝቷል፤ ወጣቶችም ያለማንም ጉትጎታ በሚችሉት አቅም ሁሉ በበጎ ፍቃደኝነት አገራቸውንን ህዝባቸውን ለማገዝ እየሰሩ ነው። ይህ እንግዲህ የማህበሩ የስራ ውጤት ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል በማለት ይገልጻል።

ወጣቶች በተለይም በመንግስታዊና በትልልቅ ተቋማት ላይ ሊኖራቸው የሚገባውን የመሪነት ስፍራ ላይ መንግስትም ተቃዋሚ ፓርቲዎችም ሊያስቡበት ይገባል በማለት የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ተደርገዋል፤ ይህ ሁኔታም አሁን ላይ ፍሬ አፍርቶ በርካታ ወጣቶች በትልልቅ የመንግስት የስራ ኃላፊነቶች ላይ እየታዩ ነው ብሏል።

ይህም ቢሰራ ዛሬም ድረስ የወጣቶች ጥያቄ ተፈቶ አላለቀም በርካታ ወጣቶች በአገራቸው ላይ ሰርቶ የመለወጥ ተስፋቸው ተሟጦ ስደትን እንደ ትልቅ አማራጭ እያዩት ነው፤ በዚህ ላይ እንደ ማህበር የተሄደበት ርቀት ምን ያህል ነው? ስል ላነሳሁላቸው ጥያቄ ሲመልሱም፤ "በየዘመኑ የወጣቶች ጥያቄ በተለያየ መልኩ ይነሳል እያደገም ይመጣል፤ አሁንም ያለው ሁኔታ በተለይም ከተለያዩ የትምህርት ተቋማት ተመርቀው ከወጡ በኋላ የስራ እድል የማግኘቱ ሁኔታ የጠበበ ነው፤ በሌላ በኩል የራሳቸው ፈጠራ ኖሯቸው እሱን እንኳን ወደተግባር ቀይረው በመስራትና በመለወጥ ሂደት ላይ እጥረቶች አሉ፤ እኛ እንደ ማህበር ስራን ፈጥረን የምንሰጥበት እድል የለንም ፤ ነገር ግን በወጣቶች በኩል ያሉ ክፍተቶችን ደፍነን ለስራ ዝግጁ የማድረግ ሁኔታ ይሰራል" ይላል።

ወጣት ይሁነኝ አክሎም ማህበሩ በአደረጃጀቱ ውስጥ የአቅም ግንባታና የኢኮኖሚ ዘርፍ አለው፤ በዚህ ውስጥ ደግሞ በዓመት ውስጥ ምን ያህል ወጣቶች የስራ እድል ሊፈጠርላቸው ይገባል? የሚለውን በመያዝ የአመለካከት ቀረጻ ላይ ስልጠና ይሰጣል፤ በፍላጎታቸው ከታችኛው የስራ እርከን ተነስተው ከፍ ወዳለው ደረጃ የሚደርሱበትን ሁኔታ በማስተማር ብቁ አድርገን በተለይም በአካባቢያቸው ያሉ ምቹ ሁኔታዎችን እንዲያዩ ተጨማሪ ነገሮችንም ከአዲስ አበባ ጥቃቅንና አነስተኛ ቢሮ ከአዲስ አበባ የስራ እድል ፈጠራ ተቋም ጋር እያገናኘን ብድር የሚመቻችበትን የመስሪያ ቦታ የሚያገኙበት ሁኔታ እንዲፈጠርላቸው የድጋፍ ደብዳቤ በመጻፍ ራሳችንም ተገኝተን በማወያየት የወጣቶችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ በመደበኛነት የምንሰራው ስራችን ነው።

እንደ ማህበር ወጣቶች ስንል በጠቅላላው ወንዶችንም ሴቶችንም ያጠቃልላል፤ ነገር ግን ሴቶች ደግሞ ከወንድ በተለየ ሁኔታ ትኩረት ሊያገኙ ይገባቸዋል በማለት ከወረዳ ጀምሮ እስከ ከተማ ድረስ ሴቶችን በምን ያህል ደረጃ ተሳታፊ እያደረጋችሁ ነው የሚለውን እናያለን፤ በዚህም የሴቶች ተሳትፎ እንዲጠናከር ውክልናቸውም እንዲጎለብት ጥረት እናደርጋለን፤ በስብሰባዎቻችን በበጎ ፍቃድ በተግባሮቻችን የሴቶች ተሳትፎ እንዲጠናከር ውክልናቸው ከፍ እንዲል እናደርጋለን። እዚህ ላይ ግን ሴቶችን ብቻ ሳይሆን አካል ጉዳተኛ ወጣቶችም እንዲሳተፉ እናደርጋለን።

ይህ የወጣቶች ተሳትፎም ሆነ የማህበሩ ጥረት ግቡን ሊመታ የሚችለው አገር ሰላም ስትሆን ነው። በአገሪቱ ላይ ለአንድ ቀን የሚፈጠር ችግርን ለወጣቱ አንድ ዓመት ከህይወቱ ላይ ያጎላል። በመሆኑ ወጣቱ የአካባቢውን አልፎም የአገሩን ሰላም በመጠበቅ ውስጥ ግንባር ቀደም ተሳታፊ ሊሆን ይገባል። በመሆኑም በሰላም መደፍረስ ትልቁ ተጎጂ ራሱ መሆኑን ተገንዝቦ ሰላሙን መጠበቅም በእጁ ያለ ነገር ነው እንደ ወጣት ይሁነኝ ገለጻ።

በየትኛውም ዓለም ያሉ ወጣቶች ለውጥ ይፈልጋሉ፤ አዲስ ነገር ይመኛሉ፤ የነበረው ነገር የማይጥመው ወይም ደግሞ የማይመቸው ብዙ ወጣት አለ፤ ለውጥ ይጠይቃል፤ ይህንን ተገቢነት ያለውን ጥያቄ በአልባሌ ሁኔታ ሊጠቀሙ የሚችሉ አካላት እንዳሉ ተገንዝቦ መጠቀሚያ እንዳያደርጉት ተጠንቅቆ ጥያቄውን መዝኖ ሁኔታዎችን አጥንቶ ማቅረብ እንዲችል ውይይቶች ይደረጋሉ። ከሚመለከታቸው አካላት ጋርም ወጣቶችን ወክለን ጥያቄዎችን እናቀርባለን። ከዛ ባሻገር ደግሞ የአካባቢው ዘብ ሆኖ እንዲቆም የማድረግ ስራም ይሰራል ይላል ወጣት ይሁነኝ።

" ወጣቶች የእነሱን ጥያቄ ተገቢ ባልሆነ መንገድ ሊጠቀሙ የሚችሉ አካላትን ተረድተው በምክንያታዊነት ጥያቄዎችን እንዲያቀርቡ በየጊዜው ውይይቶች ይዘጋጃሉ የሚነሱ ጉዳዮችንም ወጣቶችን በመወከል እንዲቀርቡ እናደርጋለን፤ ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ ወጣቱ በንቃት ራሱንም አካባቢውንም እንዲጠብቅ ማድረግ የማህበሩ ትልቅ ስራ ነው። ይህም ባለፉት ጊዜያት አገር ችግር ላይ በነበረችበት ወቅት ተደራጅቶ አካባቢውን በመጠበቅ በኩል ያሳየው ሚና ለዚህ ተጠቃሽ ነው" ይላል ወጣት ይሁነኝ።

ማህበሩ እንደ ተቋም በክፍለ ከተሞች እንዲሁም ወረዳ ላይ ጽህፈት ቤቶችን ከፍቶ እቅድ አውጥቶ በዛ እየተመራ ስራውን የሚያከናውን ነው ያለው ወጣት ይሁነኝ ከዚህ አንጻርም በክፍለ ከተሞች አካባቢ የስራ እድል ተፈጠረ ሲባል በተጨባጭ ለምን ያህል ወጣቶች በምን ዘርፍ ተፈጠረ የሚለውን የምንገመግምበት አሰራር አለ፤ በዚህም በመንግስት ነው ወይስ በግል የሚለውን እናጣራለን ወጣቶቹ በምን መስፈርት ተመለመሉ የሚለውም ይታያል።

" እንደ አገር የሰላምና ጸጥታ ችግር ሲፈጠር ጉልበት የሚጠይቁ የልማት ስራዎች ሲታሰቡ ወጣቶችን የመፈለግ ቅድሚያ የመስጠት ሁኔታ ይስተዋላል ነገር ግን አብቅቶ ኃላፊነት መስጠት ላይ እንዲሁም ለሚያነሳው ጥያቄ ዘላቂ የሆነ መልስን መስጠት ላይ የሚሰሩ ስራዎች አመርቂ አይደሉም። በሌላ በኩል ደግሞ አሁን ላይ የወጣቶች የስራ እድል ፍላጎት ጥናትን መሰረት አድርጎ የሚሰራ አይደለም። የላስቲክ ሱቅ በመስጠት የስራ እድል ፈጠርን በማለት ሪፖርት ይደረጋል፤ ይህ የተፈጠረው ነገር ግን ቋሚ ነው ጊዜያዊ የሚለው አይታይም፤ ይህ ደግሞ አሰራሩን ፍትሃዊ አያደርገውም። በመሆኑም መንግስት ማረም የሚገባውን ነገር ማረም የሚመለከታቸው አካላትም የሚሰሩትን ስራ ጥናት የተደገፈ ሊያደርጉት ይገባል" በማለት ወጣት ይሁነኝ ያብራራል።

ማህበሩ እስከ አሁንም ሲያደርግ እንደመጣው የቀጣይ እቅዱም የወጣቱን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ነው፤ የሚለው ወጣት ይሁነኝ ወጣቱ ሰላማዊ ጤናማ ብቁና ተተኪ በመሆን አገሩን የበለጸጉት አገራት የደረሱበት ደረጃ ላይ የሚያደርስ እንዲሆን አቅደን እንሰራለን።

በሌላ በኩልም የወጣቶችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት በማረጋገጥ የሚገባውን ቦታ እውቀትና የትምህርት እድል እንዲያገኝ ማድረግ ደግሞ የእቅዳችን አካል ነው።

"....ወጣቶች አቅሜ ክህሎቴ ምንድን ነው? የሚለውን ማየት ምን ብሰራስ ከራሴ አልፌ ለሌሎች እንዲሁም ለአገር ልጠቅም እችላለሁ ይህንን ለማድረግስ ምን ዓይነት ድጋፍ ከማን ማግኘት አለብኝ የሚለውን ነገር መመርመር ያስፈልገዋል" በማለት ወጣት ይሁነኝ ሀሳቡን አጠቃሏል።

# የምድር በረከት

## የኢትዮጵያን የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ለማልማት የተሄደባቸው ርቀቶች

**ስምስም መንግሥቱ**

በማዕድን ሚኒስቴር መስሪያ ቤት እገኛለሁ። በስፍራው "ማይኒንግ ጋለሪ" እየተባለ የሚጠራውን የማዕድን ሙዚየም ለመመልከት ነው በቦታው የተገኘሁት። በሙዚየሙ ውስጥ በተለምዶ "ደበኛን" እያልን በምንጠራቸው የተለያየ መጠን ባላቸው ጠርሙሶች ውስጥ "በፈሳሽ" መልክ የተለያዩ ናሙናዎች ለእይታ ቀርበዋል። ከፈሳሹ አንደኛው የምግብ ዘይት የሚመስል መልክ ያለው ሲሆን፣ ሌላኛው ደግሞ ጥቁር ነው። የተጣራና ያልተጣራ ይሆናል ብዬ ገመትኩ። ነገር ግን ጥቁሩ ነዳጅ ሲሆን የምግብ ዘይት የሚመስለው ደግሞ የተፈጥሮ ጋዝ መሆኑን ከባለሙያ ማብራሪያ ተረዳሁ። የተመለከትኳቸው ነገሮች በኢትዮጵያ የተፈጥሮ ነዳጅ መኖሩን ለማረጋገጥ ቁፋሮ ተካሂዶ የተወሰዱ ናሙናዎች ናቸው።

በሌላ ክፍል ውስጥ ደግሞ በውጭ ኩባንያዎች ቁፋሮ ተካሂዶ የተገኘውና በተለያየ የመረጃ አያያዝ ዘዴ ገላጭ ጽሁፍ ተደርጎበት የተደራጀ መረጃ ይገኛል። ክፍሉም "ዳታ ቤዝ ኮር ሀውስ" ይባላል። በዚህ ክፍል ውስጥ በእጄ ነካክቼ ያየሁት ድንጋይ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ፍለጋ ቁፋሮ ተካሂዶ የተገኘና የነዳጅ ሀብት ስለመኖሩ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ነው። ተደራጅተው የተቀመጡት መረጃዎች ለማልማት ፍላጎት ያለው ኩባንያ ሲገኝ በቀላሉ መረጃ እንዲያገኝ የሚረዱ ናቸው። ኩባንያዎች የኋላ ታሪኩን ይዘው የራሳቸውን ጥናት ጨምረውበት ወደ ተግባር ለመግባት የሚያስችላቸው እንደሆነ ለመረዳት አያዳግትም።

በኢትዮጵያ የተፈጥሮ ነዳጅና ጋዝ መኖሩን የሚያረጋግጥ የተደራጀ መረጃ በሚገኝበት "ዳታቤዝና ኮር ሀውስ" ውስጥ በውጭ ኩባንያዎች በተለያየ ጊዜ ከተሰበሰቡት መረጃዎች መካከል በደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ የሚገኘው ኦጋዴን ቤዚን መረጃ ይጠቀሳል። ለአብነትም ሲንክሌር (Sinclair) በተባለ ኩባንያ እ.አ.አ ከ1945 እስከ 1956፣ ኤልዋርዝ (elwareth) በተባለው ኩባንያ ከ1959 እስከ 1967፣ በቴኔኮ (tenneco) ኩባንያ ከ1969 እስከ 1974 ደግሞ ኋይትስቶን (Whitstone) ኩባንያ ከብዙዎቹ መካከል ጥቂቶቹ ናቸው።

በአማራ ክልል ወሎ ወረኢሉ አካባቢ በአባይ ቤዚን እ.አ.አ ከ2008 እስከ 2014 ፋልከን ፔትሮሎየም ሊሚትድ (palken petroliam limited) በተባለ ኩባንያ የተሰበሰበ መረጃ እንዲሁም ቤሲፕ ፍራንላፕ (Beciep franlap) በተባለ የፈረንሳይ አማካሪ ኩባንያ እኤአ ከ1985 እስከ 1998 በአጠቃላይ የተጠናቀረ የኢትዮጵያ የነዳጅ አለኝታ መረጃ በክፍሉ ውስጥ ይገኛል።

እንዲህ መረጃዎቹን ተዘዋውሬ ባየሁ ጊዜም "የኢትዮጵያ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ለምቶ መቼ ይሆን የአገር ኢኮኖሚ ዋልታና ማገር የሚሆነው?" የሚለው የብዙዎች ጥያቄ በእኔም ውስጥ ሲመላለስ ነበር። በኢትዮጵያ የነዳጅ ሀብት ዙሪያ በኩባንያዎች የተሰበሰቡ መረጃዎችን አደራጅቶ ማስቀመጥ ወደ ልማቱ ለመግባት ጥሩ መንደርደሪያ ነው። እሱ ብቻውን ግን በቂ ነው ማለት አይቻልም። ይህን ሀብት አልምቶ ጥቅም ላይ ማዋል ያስፈልጋል።

እስከ አሁን ባለው ሁኔታ ግን ይህን ሀብት አልምቶ መጠቀም አልተቻለም። ሃብቱን አልምቶ ወደ ምጣኔ ሃብታዊ አቅም ላለመቀየር እንደ ምክንያት ከሚነሱት ውስጥ አንዱ የአገር ውስጥ ወቅታዊ የፖለቲካ ሁኔታ ነው። ዓለም አቀፍ የነዳጅ ኩባንያዎች የሚያደርሱት አሉታዊ ተጽእኖም ሌላው ምክንያት ነው። ወደ ልማቱ በፍጥነት ለመግባት የሚያስፈልገው መዋእለ ነዋይ ከፍተኛ መጠን ያለው መሆኑም ሌላኛው ምክንያት ነው። በዘርፉ ብቁ ባለሙያ ከማስፈለጉም ባሻገር ሰላምና መረጋጋት፣ የመንግሥት ቁርጠኝነትም ወሳኝ መሆናቸው በሌላ በኩል ይነሳል። በእነዚህ ምክንያቶች የኢትዮጵያ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሀብት አንዴ ተስፋ ሰጪ ውጤት ሲያስመዘግብ ሌላ ጊዜ ደግሞ ወሬው ደብዛው እየጠፋ ማነጋገሩን እንደቀጠለ ነው።

በስፋት ከሚነሳው በደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ የሚገኘው የኦጋዴን ቤዚን ነዳጅ ቀጥሎ በአማራ ክልል ወሎ ወረኢሉ አካባቢ መሬት ሰንጥቆ ያለከልካይ እየፈሰሰ ስለመሆኑ ተደጋግሞ የተነሳ ጉዳይ ነው። በተለይ በአባይ



**እጩ ዶክተር ተፈራ ዓለሙ፤**

ቤዚን መሬት ሰንጥቆ የወጣው የተፈጥሮ ጋዝ ጉዳይ ሲያነጋግር ቆይቷል። በዚህ አካባቢ ስላለው ነባራዊ ሁኔታና አጠቃላይ በተፈጥሮ ጋዝ ሀብት ዙሪያ ዘርፉን የሚመራውን የማዕድን ሚኒስቴር የሚመለከተውን ባለሙያ አነጋግረናል። በሚኒስቴሩ ከፍተኛ የፔትሮሊየም ባለሙያና በአሁኑ ጊዜም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፒኤችዲያቸውን እየሰሩ ያሉት አቶ ተፈራ ዓለሙ የሰጡንን ማብራሪያ ይዘን ቀርበናል።

አቶ ተፈራ የጂኦፊዚክስ ባለሙያ ናቸው። በቅድሚያም ሙያውን መሠረት ያደረገ ማብራሪያ ሰጥተውናል። እርሳቸው እንዳሉት፤ ጂኦፊዚክስ የመሬት ውስጥ ሃብት አያያዝና አፈጣጠርን የሚያጠና ዘርፍ ሲሆን፤ በመሬት ውስጥ ምን አይነት የተፈጥሮ ሀብት እንዳለ ወይንም እንደሚገኝም ያጠናል። ከዚህ ውስጥም ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ይጠቀሳሉ።

ከዚህ አኳያም ኢትዮጵያ ፔትሮሊየም መገኛ ምቹ የሆኑ ወደ ስድስት አካባቢዎች አሏት። እነርሱም ኦጋዴን፣ አባይ፣ መቀሌ፣ ጋምቤላ፣ መተማ፣ ስምጥሸለቆን ተከትሎ ደግሞ ሪፍትቫሊ ቤዚን ናቸው። ከነዚህ መካከልም በስፋት ጥናት የተካሄደውና ጥሩ የሚባል ደረጃ የደረሰው የኦጋዴን ቤዚን ነው። አባይ ቤዚንም ቢሆን ከኦጋዴን ቤዚን ባልተናነሰ ይጠቀሳል። በእነዚህ አካባቢዎች ያለው የፔትሮሊየም ሀብት ክምችት ከፍተኛ እንደሆነ መረጃዎች ቢያመላክቱም፣ ሀብቱ ሰፊ የጥናት ሥራ ማድረግን ይፈልጋል።

በዘርፉ ጥናት የመስራትና ወደ ትግበራ የመግባት ጉዳይን አስመልክቶ አቶ ተፈራ እንደገለጹት፤ የጥናት ሥራዎች የሚደረጉት በውጭ ኩባንያዎች ወይንም ባለሀብቶች ሲሆን፣ በእዚህ በኩል ለአብነትም የአሜሪካ፣ የሩሲያ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በቻይና ኩባንያዎች ይጠቀሳሉ። እነዚህ የነዳጅ ፍለጋ ጥናት ሥራዎች አብዛኛውን ጊዜ ቀጣይነት የላቸውም። ለእዚህ በምክንያት ከሚጠቀሱት ውስጥ ደግሞ የመሪዎች መለዋወጥ ወይንም አገራዊ ለውጥ አንዱ ነው፤ ይህን ተከትሎም የኩባንያዎች አብሮ መክሰም እንደሚያጋጥማቸው ይገልፃሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ኩባንያዎች በገንዘብ አቅም ውስንነት ሥራውን አቋርጠው ይወጣሉ። የኩባንያዎች መለዋወጥና የተለያዩ ምክንያቶች የዘርፉ ሥራ ዘላቂና ተከታታይ እንዳይሆን አድርጎታል። ይህም ሆኖ ግን በየወቅቱ ከየኩባንያዎቹ የተገኙት መረጃዎች ተደራጅተው ይያያዛሉ። ከላይ ከተጠቀሱት ምክንያቶች ባሻገርም ከፖሊሲ ጋርም የሚያያዙ አንዳንድ ውስንነቶች ለጥናትና ትግበራው አለመሳካት የራሳቸውን ሚና ይጫወታሉ።

"ያለፉ ተሞክሮዎች ይህን የሚያሳዩ ቢሆኑም አሁን ደግሞ ዘመኑ ተለውጧል" የሚሉት አቶ ተፈራ፤ አገር ማደግ የምትችለው ባለው የተፈጥሮ ሀብት ላይ እንደሆነ መነሻ በማድረግ መንግሥት ለዘርፉ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑን አመልክተዋል። በዚሁ መሠረትም ሀብቱን መለየትና በምን ደረጃ ሊለማ እንደሚችል አቅጣጫ ተይዞ እየተሰራ እንደሆነ ነው የጠቆሙት።

ለአሰራር ምቹ እንዲሆን የፍለጋና የማስተዳደር ሥራ የሚያከናውን ክፍል መለየቱን የሚናገሩት የጂኦፊዚክስ ባለሙያው፤ በዚሁ አሰራርም እርሳቸው የሚገኙበት ክፍል በዘርፉ ለመሰማራት ጥያቄ የሚያቀርቡ ኩባንያዎች ሲመጡ እንደሚያስተናግድ ይገልፃሉ። ወደ ሥራም ሲገቡ ክትትልና ድጋፍ እንደሚደረግላቸው ያስረዳሉ።

ክፍሉ ከዚህ በተጨማሪም በኩባንያዎቹ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ያደራጃል ያሉት ባለሙያው፣ ለማልማት ፍላጎት ያላቸው ኩባንያዎች ሲመጡም መረጃውን እንዲያገኙ በማድረግ ወደ ልማቱ የሚገቡበትን ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥርም ያብራራሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ እስካሁን በተከናወነው ሥራም በኢትዮጵያ የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ፍለጋ ከተለያዩ አገራት የመጡ ብዛት ያላቸው ኩባንያዎችን ማስተናገድ ተችሏል። ኩባንያዎቹም ጥሩ የሚባል ሥራ ሰርተዋል። በአጠቃላይ በዘርፉ እንደ አገር በተሰራው ሥራ በኦጋዴን ቤዚን አካባቢ ለተፈጥሮ ጋዝ ፍለጋ ከ670 በላይ የጉድጓድ ቁፋሮዎች በማከናወን የፍለጋ ስራ ተሰርቷል። ከዚህ ውስጥ 19 የሚሆኑት ለምርት የተዘጋጁ ጉድጓዶች መሆናቸው ተረጋግጧል።

እንደ አቶ ተፈራ ገለፃ፤ በደቡብ ኦሞ አካባቢ "ታሎ" የሚባል የእንግሊዝ ኩባንያ ወደ አራት ጉድጓዶች በመቆፈር የሰራው ሥራም ይጠቀሳል። ይሁን እንጂ አመርቂ ውጤት ባለማግኘቱ ሥራውን ለማቋረጥ ተገድዷል። ቀጣይ ሥራዎች ቢሰሩ ግን ውጤት እንደሚገኝበት በኩባንያው በተሰራው ሥራ የተገኘው መረጃ ያሳያል።

አርባ ምንጭ አካባቢም አንድ ኩባንያ የጂኦፊዚክስ ጥናቶችን አከናውኖ ሊቆፈር የሚችል ቦታ ከለየ በኋላ በገንዘብ እጥረት የቁፋሮ ሥራው ሳይካሄድ ቀርቷል። የዚህም መረጃ የሚያሳየው ሊመረመር የሚችል መሆኑን ነው። አቅም ያላቸው ኩባንያዎች በሥፍራው ላይ ቢሰሩ ውጤት ማግኘት እንደሚችሉ አመላካች ነገር መኖሩን ነው መረጃው አሳይቷል። ጋምቤላ ክልል ውስጥም እንዲሁ ሁለት ጉድጓዶች ተቆፍረዋል። ደቡብ ሱዳን አካባቢ ያለውን የተፈጥሮ ጋዝ መነሻ በማድረግ ኢትዮጵያ ውስጥም ሀብቱ ሊኖር ይችላል በሚል በአካባቢው ላይ ሙከራው ተደርጓል። ቁፋሮው የተከናወነበትና የማእድን ሀብቱ ይኖራል ተብሎ የተገመተበት አካባቢ ባለመጣጣሙ ለጊዜው ሥራው ተቋርጧል።

የጂኦፊዚክስ ባለሙያው በአባይ ቤዚን የተፈጥሮ ጋዝ ስለመኖሩ ምልክቱ የታየው ፋሽሽት ጣሊያን ኢትዮጵያን በኃይል በወረረበት ወቅት ስለመሆኑ መረጃዎችን ዋቢ አርገው ይጠቅሳሉ። እንደ አንደእሳቸው ገለጻ፤ በወቅቱ የነበረው መረጃም በትክክል ሀብቱ የተገኘበትን ሥፍራ አላመላከተም። ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ እኤአ በ1979 ባለሙያ በስፍራው ልኮ ባካሄደው ጥናት አካባቢው ላይ በሳይንሱ መጠሪያ "ማቹርድ ነዳጅ" የሆነ የተፈጥሮ ጋዝ መገኘቱን አረጋግጧል። መረጃው ከየትኞቹ የአለት አይነቶች እንደተገኘም በወቅቱ ለማጠናቀር ተችሏል።

ከዚያ በኋላም "ቤሲፕፍራንላፕ" የተባለ የፈረንሳይ ኩባንያ ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ የተፈጥሮ ጋዝ ሀብት ዙሪያ በተለያዩ ኩባንያዎች የተደረጉ የፍለጋ ጥናቶችን አሰባስቦ የኢትዮጵያ የነዳጅ አለኝታ ‹‹petroleum potential of Ethiopia›› በሚል ስለሀብቶቹ አይነት፣ የሚገኙባቸውን ሥፍራዎች፣ በምን ደረጃ ላይ እንደሆኑና ምን ሊደረጉ እንደሚችሉ ጭምር ምክረሀሳብ ያካተተበት መረጃ በሚኒስቴሩ ይገኛል። እኤአ በ1998 የተደረገው ጥናት እንደሚያሳየው ወሎ ወረኢሉ አካባቢ የተገኘው ነዳጅ ሀብት የትኛው የአለት አይነት አመንጪ እንደሆነ፣ የነዳጁ አይነትና መረጃው በሙሉ ተካትቷል። መረጃው የተሰሩትን ሥራዎች ለማሳየት ከማገዙ በተጨማሪ ሀብቱን በማስተዋወቅ በልማቱ የሚሳተፉ ኩባንያዎችን ወይንም ባለሀብቶችን ለመሳብ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው።

እነዚህን መረጃዎች መሠረት አድርጎ "ፋልከን ፔትሮሊየም" የተባለ ኩባንያም የአባይ ቤዚን ሶስት ከፍሎችን (ብሎኮች) ለማጥናት ከማዕድን ሚኒስቴር ፈቃድ ወስዶ ተጨማሪ ሥራ ሰርቷል። ኩባንያውም በአካባቢው "ኮንአቦን" እና "ወረኢሉ" በሚባሉ አካባቢዎች ሊቆፈር የሚችሉ ሁለት ቦታዎችን ለይቷል። በአካባቢዎቹ ላይ እስከ ሁለት ቢሊየን በርሜል የሚገመት ነዳጅ ሊኖር እንደሚችል የኩባንያው መረጃ አመልክቷል። ኩባንያውም ይሄን ሀብት ለማግኘት ሲሰራ የቆየ ቢሆንም፣ በገንዘብ አቅም ማነስ ባለመቀጠሉ ውጤቱን ማየት አልተቻለም። በአሁኑ ጊዜ መሬቱን ሰንጥቆ ወጥቶ ለገሂዳ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ላይ እየፈሰሰ የሚገኘው የተፈጥሮ ነዳጅ ዋና የመገኛ ሥፍራው ሌላ ቦታ ነው። ዋና የመገኛ ስፍራዎቹ ኮንአቦንና ወረኢሉ የሚባሉት አካባቢዎች ነው።

"ሥራዎች እየተጀመሩ የሚጓተቱና የሚቀሩ ከሆነ የሚፈለገው ውጤት ላይ እንዴት መድረስ ይቻላል? በሚኒስቴሩ በኩል ሊደረግ የሚችል እገዛስ የለም ወይ?" የሚል ጥያቄ ለአቶ ተፈራ አነሳንላቸው። እሳቸው በሰጡትም ምላሽ፤ ኩባያዎች ለሥራ የሚያስፈልጋቸውን ከቀረጥ ነፃ ወደ አገር ውስጥ እንዲያስገቡ መንግሥት መፍቀዱን፣ ባለሙያዎቻቸውንም ይዘው እንዲመጡና በህግ በኩል ኩባንያው ውጤታማ ሆኖ እንዲጠቀም የሚያስችለው ምቹ ሁኔታ መኖሩን አስታውቀው፣ እነዚህ ሁሉ ለኩባንያዎቹ ድጋፍ መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

በነዳጅና በተፈጥሮ ጋዝ በኩል ወደ ልማት የተቀየረ ነገር ባይኖርም፣ በፍለጋ ግን ጠንካራ ሥራ መሰራቱን የገለጹት አቶ ተፈራ፤ ዘርፉን ለማልማት የገንዘብ አቅምና ባለሙያም የሚፈልግ እንደሆነ ይገልፃሉ። በአገር አቅም የሚቻል ባለመሆኑ አቅሙ ባላቸው የውጭ ኩባንያዎች ላይ የተወሰነ እንደሆነም ይናገራሉ። አቅም ኖሯቸው የሚመጡ ኩባንያዎችም በገንዘብ አቅም ተፈትነው የሚመለሱበት ሁኔታ እንደሚያጋጥም ተናግረዋል።

ኩባንያዎች የማእድን ሀብቱን ካገኙ በኋላ ከልማቱ የመጋራት መብት እንኳን እያላቸው በስራው ያልቀጠሉበት ሁኔታ ጥያቄ ሊያጭር ይችላል። ያም ሆኖ ግን ተስፋ ሳይቆርጡ ፍለጋውንም ወደ ልማቱ የሚገባ ባለሀብት ማፈላለግ ላይም ጠንክሮ መስራት የግድ ይላል። በተለይ ደግሞ እንደ አገር ያሉ ተግዳሮቶችን መፈተሽም ይጠበቃል።

ከተግዳሮቶች አንዱ የሆነውን አገራዊ ለውጥ ሲኖር ወይንም መሪዎች ሲለዋወጡ የልማት ሥራውም አብሮ እንደነባራዊው ሁኔታ የሚለዋወጥ ሁኔታ እንዳይኖር በማድረግ ወይም ስራው ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግ ላይ ጠንከር ያለ ሥራ መሰራት እንዳለበት ባለሙያው ያስገነዝባሉ። የተፈጥሮ ጋዝ ሀብት ለኃይል ፍጆታ ብቻ ሳይሆን በግብርናው ዘርፍ ለማዳበሪያም ግብአት የሚውል ዘርፈብዙ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የሚያስገኝ መሆኑን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱም በማመን ለማዳበሪያ ግብአት እንደውል እያጠና መሆኑን አመልክተዋል። በዘርፉ ቀደም ሲል ተደራጅተው የተቀመጡትን መረጃዎች በማስተዋወቅ ኩባንያዎችን የመሳብ ሥራም መጠናከር እንዳለበት ገልጸዋል።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## ሴት የወንድ ጌጥ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ወንድ ልጅ እንደሴት ልጅ ምን ጌጥ አለው? እግዜር እንደሴት የተዋበ ምን ፈጥሯል? ከትላንት እስከዛሬ ዓለም በሁለት ኃይሎች ስር ናት እላለው..በሴትና በውበት፡፡ ዓለም የሴትን ውበት ተደግፋ እንደቆመች የገባኝን ያክል ምንም አልገባኝም፡፡ ምድር ላይ እንደ ሴት ልጅ ቀምሼው የጣመኝ ጣፋጭም የለኝም፡፡

እነ ስምረት ግቢ ተከራይቼ ነው የምኖረው፡፡ ግቢው ውስጥ ሰባት የሚከራይ ክፍል አለ..ከሰባቱ ክፍል ስድስቱ የተያዘው በሴቶች ነው..በላጤ ሴቶች፡፡ እዛ ግቢ ስገባ ገነት የገባሁ ነበር የመሰለኝ፡፡ በህይወቴ መቼም ከማላገኘው እድል ጋር የተገናኘሁ ያክል ነበር የተሰማኝ፡፡ ገነት ምን ትመስላለች ላለኝ የነስምረት ግቢ እለዋለው፡፡ ገነት ምን ትመስላለች ላለኝ ሌላም የምመልሰው አንድ መልስ አለኝ..በተዋቡና በቆነጁ ሴቶች መሀል መገኘት የሚል፡፡ ምድር ላይ ደጋግሜ ብፈጠርም ይሄን እውነቴን የሚሽር እውቀት እንደማይኖር አምናለው፡፡ ሴት የወንድ ገነት ናት..ወደምድር የመጣባት..ባዝኖና ተንከራቶ ከምድር የሚሄድባት፡፡ ሴት የወንድ ልጅ አዲስ ነገሩ ናት..ሴት በወንድ ነፍስ ውስጥ አሮጌ ሆና አታውቅም፡፡

ስድስት ሴቶች ወዳሉበት ግቢ በተከራይነት ገባሁ፡፡ መቼም እንደዛ ቀን ያለ የሙላት መንፈስ ጎብኝቶኝ አያውቅም፡፡ ደስታዬ በሴቶች መኖር ላይ መንጠልጠሉ ብዙ ቀን መከፋትን ቢፈጥርብኝም ግን ከዛ እውነት መሸሽ አልቻልኩም፡፡ ዓለም ላይ ወንዶች ጠፍተው እኔና እልፍ ሴቶች ብንቀር የምመኝ አይነት ወንድ ነኝ፡፡ ከአምስቱ ጋር ተግባባሁ..ምዕተ ዓመት ያስቆጠረ የሚመስል ትውውቅ ፈጠርን፡፡ እጅግ ሲበዛ መልካምና ተጫዋች የሆኑ ሴቶች ናቸው፡፡ በተለይ ሩታና ሳሮን የውስጥ ሽሚዜን ያክል የቀረብኳቸው ሴቶች ሆኑ፡፡ አደይና ኤማንዳም ህይወት የሚያጣፍጡ ቅመሞች ሆነው ወደህይወቴ መጡ፡፡ ማከዳ ጭምትነት ቢይዛትም ባለሁበት ሁሉ ነበረች፡፡ ቤቴ የበላሁበት ጊዜ ትዝ አይለኝም..ዛሬ አንዷጋ ነገ አንዷጋ እያልኩ የገነት ህይወቴን ተያያዝኩት፡፡ ምግብ ማብሰል እንደምችልና ጎበዝ እንደሆንኩ ስነግራቸው ባላማመን ከመወድስ በቀር ሁሉም የሰራሁትን ቀምሰውታል፡፡

ከጎኔ ካለችው መወድስ ጋር ግን ምንም አናወራም፡፡ እኔን ስታይ ሴይጣኗ ይመጣል መሰለኝ..የዝምታ ጋኔኗ የሚነሳው ያኔ ነው፡፡ ስቃና ተጫውታ እኔጋ ስትደርስ ዝም የሚያሰኝ የሆነ ጋኔን አለባት፡፡ ዝምታዋን ግን እወደዋለው፡፡ ዝምታዋን ስለምወደው ዝም እንድትል ያደረጋትን ጋኔን እካድመው ጀመር፡፡ ጋኔን ስወድ..ጋኔን ሳፈቅር መወድስ የመጀመሪያዬ ናት፡፡ ከእሷ ውጪ ማንም የማይችለው ደስ የሚል ዝምታ አላት፡፡ ዝምታዋ ውስጥ ካልሆነ ወሬዋ ውስጥ ብርቅ ሆናብኝ አታውቅም፡፡ በሳቋ ውስጥ ያን ያክል ናት፡፡ ከዚህም በላይ ዝም እንድትል ፈጣሪ ልሳኗን እንዲዘጋው ተመኝቼ አውቃለው፡፡ ሁሉም ቀርቶብኝ ለምን እንደምትጠላኝ ብቻ ባውቀው እላለው፡፡ እሷን አልፌ ሩቅ ካሉት ሳሮንና ሩታ ጋር ድንበር አልፌ ሳወራ በር ላይ እቃ እያጠበች ዝም ትለኛለች፡፡ እሷን አልፌ የሚቀጥለው ክፍል ካሉት ኤማንዳና አደይ ጋር በርበሬና ጨው ስዋዋስ የጆሮ ማዳመጫዋን ሰክታ ልብስ እያጠበች ትዘጋኛለች፡፡ ይቺን ሴት ጎኔ ስላደረጋት ፈጣሪን ወቅሼው አላውቅም፡፡ እንኳንም ጎረቤቴ ሆነች ስል ሰማይ አይቼ አውቃለው፡፡ ስወጣና ስገባ ዝም ያለ ፊት እጣ ክፍሌ ሆኖ ህይወት ቀጠለ፡፡

ጠዋት ወደ ስራ ልሄድ በሬን ስከፍት ጥርሷን እየፋቀች ከነዝምታዋ አገኛታለው፡፡ ዝም ባለው ንጋት ውስጥ ዝም ብላ ሳያት ገና ያልነጋ መዐልት ትመስለኛለች፡፡ ከለሊቱ አስራ አንድ ሰዐት የሚመስል ፊት አላት..ሊነጋ ያለ ቀይዳማ ፊት፡፡ ዝምታዋ ይጥመኛል፡፡ የትም ሰምቼው ከማላውቀው ከሳሮንና ከኤማንዳ ሳቅና ድምጽ በላይ የእሷ ዝምታ ደስታዬ ነው፡፡ ኩራቷ ይስበኛል..የትም ጠርኖኝ ከማያቀው ከአደይና ከሩታ ሽቶ በላይ ኩራቷ ይማርከኛል፡፡ ከመወድስ ዝምታ ተነስቼ ሴት ሲኦልም ናት ስል እንዳስብ አደረገኝ፡፡ አንዲት ውብ ሴት ጎንህ ሆና ዝም ስትልህና እንዳልተፈጠረ ስትቆጥርህ ከዚህ በላይ ምን ሲኦል አለ? ለመላዕክትነት የቀረበች አንዲት አማላይ ሴት አንተን አልፋ ከሌሎች ጋር ስታወራና ስትሳሳቅ እንደማየት ምን ገሀነም አለ? በመወድስ ዝምታ የደረስኩበት የመጨረሻው ግኝቴ ሴት ልጅ ሁሉንም መሆን እንደምትችል ነው፡፡

ከሴቶች ጋር መገልፈጤ ያላማራቸው የስምረት አባት አንድ ቀን ጠርተውኝ ‹ምንህም ደስ አላለኝ..ሴት አውል ነገር ነህ መሰለኝ..ቆፍጠን በል› ሲሉ ገረመሙኝ፡፡ ግቢው ውስጥ በተከራይ ላይ የተጣለ አንድ ማዕቀብ እንዳለ በገባሁ በመጀመሪያዋ ሰከንድ ተነግሮኛል..እርሱም የትኛዋም ሴት ተከራይ ግቢው ውስጥ ወንድ ይዛ ማምጣት እንደማትችል ነው፡፡ የነስምረት ግቢ ወንድ የማይገባበት ግቢ ነው፡፡ እኔ ራሱ የገባሁት እህቴ ውጪ አገር ለመሄድ በወጣችበት ተተክቼ ነው፡፡ እኔን ከዛ ግቢ ለማስወጣት የስምረት አባት ያላደረጉት ጥረት አልነበረም፡፡ በቤት ኪራይ ተማሮ ይወጣል ሲሉ በወር ሁለት ጊዜ ቤት ኪራይ ጨምረውብኝ ያውቃሉ፡፡ በዚህ አልሳካ ሲላቸው ‹አንተ ከገባህ ወዲህ የውሀና የመብራት ኪራይ ጨምሮብኛል ወይ ቤቱን ልቀቅ ወይ ክፍያ ጨምር› ሲሉ በሌላ ዘዴ መጡብኝ ይሄንንም ስቄ አለፍኩት፡፡ እዛ ግቢ እኔ ብቻ ነኝ ያልተገባ የቤት ኪራይ የምከፍለው፡፡ ወሩ ደርሶ የቤት ኪራይ ልሰጣቸው ወደቤታቸው ስሄድ ከብዙ ማስጠንቀቂያ ጋር ነው የሚሸኙኝ፡፡ ባለፈው ወር የገናን በአል አስመልክቼ አንኳን አደረሳችሁ ልላቸው በዛውም የኪራይ ብር ልሰጣቸው ስሄድ ‹የማልወዳቸውን አንድና ሁለት ነገር ስታደርግ ካየሁ ከቤት አስወጣሀለው› አሉኝ፡፡

‹የማይወዱት ምንድነው? ስል ካህን ፊት እንደቆመ መዕምን እጄን ወደ ኋላ አጣጥፌ ጠየኩ፡፡

‹እሱ ምንም አያደርግልህም..ያልኩህን ላለማድረግ ተጣጣር› ብለውኝ ብሩን ከእጄ ላይ የመቀማት ያክል ወስደው ዘጉብኝ፡፡ ምንድነው የማይወዱት እያልኩ ራሴን እየጠየኩ ወደቤቴ ተመለስኩ፡፡ ቆይቼ ስሰማ የስምረት አባት ወንድ ልጅ ቤታቸው እንዲገባ የማይፈልጉት ለልጃቸው ሲሉ እንደሆነ ሰማሁ፡፡ ከዛን ቀን ጀምሮ ግቢው ውስጥ ከስምረት ጋር ላለመገናኘት የማላደርገው ጥረት አልነበረም፡፡ አንዳንድ ጊዜ ለምን እንደፈለገችኝ ሳላውቅ በሬ ላይ ቆማ ስትጠራኝም ሆነ በሬን ስታንኳኳ እየሰማሁ ዝም የምልበት ጊዜ ነበር፡፡

የመወድስ ዝምታ የጣመኝን ያክል ይጎመዝዘኝ ጀመር፡፡ ገነት ነው ያልኩት ግቢ በመወድስ ዝምታ ጸለመብኝ፡፡ የአምስቱ ሴቶች ውበትና ቁንጅና ሳቅና ወሬ በመወድስ ዝምታ የደበዘዘ አለሜን ማንጻት አልቻለም፡፡ እየቆየሁ እኔም ዝም ማለት ጀመርኩ..የሚስቁልኝን ደጋግ ፊቶች እያለፍኩ በዝምታ ቤቴ ገብቼ መውጣት ጀመርኩ፡፡ እነ ሩታ ቤቴ ሲመጡ በዝምታ ነበር የማደምጣቸው..ምን እንደሆንኩ ሲጠይቁኝ ምንም እንዳልሆንኩ ከመመለስ ባለፈ የምላቸው አልነበረም፡፡ በኔ ነውር ራሳቸውን ጥፋተኛ ማድረግ ጀመሩ፡፡ በህይወቴ ያየሁት ሌላው ገነት..ቆንጆ ሴት ምንም ባላጠፋችው ጥፋት ወንድን ልጅ ይቅርታ ስጠይቅ ሆኖ ልቤ ተቀመጠ፡፡ አስቀይሜያቸው ሳበቃ ያስቀየሙኝ መስሏቸው እነዛ ደጋግ ልቦች ሸሹኝ፡፡ በአንዲት ዝምተኛ ነፍስ ግቢው ሙሉ ዝምታ ወደቀበት፡፡ ግቢው እንዳይሰማ በሚጠነቀቁ ሹክሹክታዎች ተዋጠ፡፡ የማውቀው የሳሮን ሳቅ..መቼም የሚረሳኝ የማይመስለኝ የኤማንዳ ድምጽ ከጆሮዬም ከልቤም እየደበዘዘ መጣ፡፡

እየቆየሁ ስመጣ በውስጤ የሆነ ስሜት እየተፈጠረ መጣ። ‹አይ ሰው! አልኩ ለራሴ፡፡ በፍቅርና በደግነት የከበቡኝን ነፍሶች ትቼ ፊት የነሳችኝን አንዲት ሴት እከጅል ገባሁ፡፡ በማላውቀው ስበት መወድስን አስብ ጀመር፡፡ ያቺን የተረገመች ነፍስ አፈቀርኳት፡፡ ጊዜ ሲጥል ማለት ይሄ አይደል? በዛ ዝምታዋ ውስጥ እንዴት ፍቅሬን መግለጽ እንዳለብኝ የተጠበብኩትን ጥበብ መቼም አረሳውም፡፡ የወንድ ታሪክ በሴት ጀምሮ በሴት ያበቃ ነው ስል እርግጠኛ ሆንኩ፡፡

አንድ ምሽት ቤቴ ተንኳኳ በሩን ስከፍት የስምረት አባት የደርግ መለዮአቸውን አጥልቀው በሬ ላይ ቆመዋል፡፡ ‹እንዴት አመሹ ጋሼ ትዕግስቱ! ከማለቴ..

‹ትዕግስቴ አልቋል! ነገ ጠዋት ቤቱን ለቀህ እንድትወጣ..› ብለውኝ መልስ ሳይጠብቁ ትተውኝ ሄዱ፡፡

ህይወቴ እዛጋ የቆመ መሰለኝ..ከዚያ ቀን በኋላ መኖር የሌለ መሰለኝ፡፡ የስምረትን አባት አየኋቸው ቀጥ ብሎ የተስተካከለ አዛውንት ቁመናቸው ቃሌ ከሚያልፍ ሰማይና ምድር ቢያልፍ ይቀላል የሚል መሰለኝ፡፡ በጅነና ርምጃ ለአንዴም ሳይዛነፉ ከመጡበት ደረሱ፡፡ የበረንዳውን መወጣጫ በእጃቸው ተደግፈው ሰባት የሚሆነውን ደረጃ ወደላይ ተያያዙት፡፡ የመጨረሻው ወለል ላይ እስኪደርሱ ድረስ እንዲያዩኝ በመሻት ቆሜ ሳያቸው ነበር፡፡ ግን አላዩኝም፡፡ ጀርባቸው አይን ቢኖረው ፊቴ ላይ ያለውን የስቃይ አዘቅት ያየው ነበር..ጀርባቸው አይን ቢኖረው ስል ተመኘው፡፡ ከግቢዬ ውጣ ብለው ሳይሆን ገለውኝ አስከሬኔን ወደመቃብር ስፍራ የሚሸኙ ነበር የመሰለኝ፡፡

በህይወቴ ሁሌም በምረግማት የእሮብ ማለዳ ላይ ከቤት ወጣሁ..ከእኔ መውጣት በኋላ እዛ ቤትና በእዛች ዝምተኛ ነፍስ ውስጥ ያለውን ታሪክ አላውቀውም..ግን ሁሌም ይናፍቀኛል፡፡

# ዓለም አቀፍ



## ተመድ በሱዳን ላይ የጣለውን ማዕቀብ አራዘመ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት /ተመድ/ የጸጥታው ምክር ቤት በሱዳን ላይ የጣለውን ማዕቀብ አራዘመ።

15 አባላት ያሉት የጸጥታው ምክር ቤት ማዕቀቡን እንዲሁም የመሳሪያ ሽያጭ እገዳውን እንዲከታተሉና እንዲቆጣጠሩ ስልጣን የተሰጣቸው የባለሙያዎች ቡድን ፈቃድን እስከሚቀጥለው ዓመት መጋቢት ድረስ እንዲታደስም ድምጽ ሰጥቷል።

13 አገራት የድጋፍ ድምጻቸውን ሲሰጡ ሩሲያ እና ቻይና በድምጸ ተአቅቦ አልፈውታል።

ማዕቀቡ ጊዜ ያለፈበት ነው። መሬት ላይ ያሉ ነገሮች ስለተሻሻሉ ሊነሳም ይገባል ሲሉ የቻይናው ተወካይ ዳይ ቢንግ መናገራቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

በመንግሥቱ ላይ ማዕቀብ መጣል የዳርፉርን ሁኔታ አያንጸባርቅም። የሱዳን መንግሥትንም አገሪቱን ከመገንባት፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እድገትንም እየከለከለ ነው ሲሉ የሩስያው ተወካይ ዲሚትሪ ፖሊያንስኪ ተናግረዋል።

የአሜሪካ ተወካይ ጆን ኬሊ በበኩላቸው ክትትል እና ሪፖርት ማድረግ አስፈላጊነትን መቀጠል እንዳለበት ድጋፋቸውን ሰጥተዋል።

ከሶስት ዓመት በፊት በተፈረመው የጁባ የሰላም ስምምነትን የተቀመጡ መለኪያዎችን በመጥቀስ “ሱዳን እና ህዝቦቿን ወደሚገባቸው ሰላም እና ብልጽግና ያሸጋግራል” ሲሉም ተደምጠዋል።

ሱዳን ከሁለት ዓመት በፊት በጄኔራል አብዱልፈታህ አል ቡርሃን በተመራ ጦር በሲቪል የሚመራውን የሽግግር መንግሥት መገርሰሷን ተከትሎ በምጣኔ ኃብት እና በፖለቲካዊ ቀውስ ውስጥ ትገኛለች።

ለአስርት ዓመታት ሱዳንንን የገዟት ኦማር አልበሽር በህዝባዊ አብዮት ከስልጣን ከወረዱ በኋላ ወደ ሲቪል አገዛዝ ልታደርገው የነበረውን ሽግግርም መፈንቅለ መንግሥቱ እንደገታው ቢቢሲ ዘግቧል።

## የዓለማችን ውቅያኖሶች 171 ትሪሊዮን የፕላስቲክ ምርቶችን ይዘዋል

የዓለማችን ውቅያኖሶች ቢያንስ 171 ትሪሊዮን የፕላስቲክ ምርቶችን መያዛቸውን ሳይንቲስቶች ማሳወቃቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

በውቅያኖሶቹ ላይ ጥናት ያደረጉ ሳይንቲስቶች ቡድን ኃላፊ ዶክተር ማርከስ ኤሪክሰን የፕላስቲክ ምርቶቹ የሰው ልጅ ከተጠቀመባቸው በኋላ ወደውቅያኖሱ የተወረወሩ መሆናቸውን ገልጸዋል።

የፕላስቲክ ምርት ዓሳና ሌሎች ውቅያኖስን ቤታቸው ያደረጉ እንስሳትን የሚገድል ሲሆን ፕላስቲክን ከውቅያኖስ ለማስወገድ መቶ ዓመት ሊወስድ ይችላል ሲሉ ሳይንቲስቶቹ አሳውቀዋል።

በፈረንጆቹ 2005 ውቅያኖሶች ላይ ሲንሳፈፍ የነበረው ፕላስቲክ ቁጥር 16 ትሪሊዮን እነደነበር ያስታወሰው ዘገባው፤ እርምጃ ካልተወሰደ በ2040 አሁን ካለው ቁጥር ሶስት እጥፍ ሊሆን ይችላል ሲሉ ሳይንቲስቶች ማስጠንቀቃቸውን አስነብቧል።

ባለፈው ሳምንት የተባበሩት መንግሥታት አገራት ቢያንስ 30 በመቶ ውቅያኖስን ለመጠበቅ ስምምነት ገብተዋል።

እንደ ውሃ ኮዳ ያሉ አንድ ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ የሚውሉ ፕላስቲኮች በፀሐይ ብርሃንና ‘ሜካኒካል ዲግሪዴሽን’ በተባለ ሂደት አማካይነት በጊዜ ሂደት ይበታተናሉ።

እንደ አሳ ነባሪ፣ የባህር ዔሊና ዓሳ ያሉ እንስሳት የተበታተነውን ፕላስቲክ ከተመገቡ በኋላ ሆዳቸው ስለሚሞላ በረሃብ ምክንያት ይሞታሉ።

ይህ ብቻ አይደለም የፕላስቲክ ምርት የምንጠጣው ውሃ ውስጥ ተገኝቶ ያውቃል። በጣም ጥቃቅን የሚባሉ የፕላስቲክ ምርቶች ሳንባ፣ ደም ሥርና ፕላሴንታችን ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ። ነገር ግን ሳይንቲስቶች ጥቃቅን የፕላስቲክ ምርቶች የሰው ልጅ ላይ ጉዳት ያደርሳሉ ወይ የሚለው እስካሁን ምላሽ እንዳላገኘ ይናገራሉ።



ውቅያኖሶች ውስጥ የሚገኙት የፕላስቲክ ምርቶች በ15 ዓመታት ውስጥ ከ16 ትሪሊዮን ወደ 171 ትሪሊዮን ማደጋቸውን ጥናቶች አመላክተዋል።

ከ2005 ዓመት በፊት በነበረው ጊዜ ውቅያኖስ ላይ የሚራገፈው የፕላስቲክ ምርት እጅግ አናሳ ነበር ይላሉ ኤሪክሰን።

አጥኚዎቹ እንደሚያምኑት ከ2005 በፊት በነበረው ጊዜ በርካታ አገራት የፕላስቲክ ምርት ወደ ውቅያኖስ መጣልን ይከለክሉ ነበር።

በጣም በርካታ የፕላስቲክ ምርት ያለበት ውቅያኖስ ሰሜን አትላንቲክ ሲሆን ግሬት ፓሲፊክ ጋርቤጅ ፓች የተባለው ሥፍራም በርካታ ፕላስቲክ ተገኝቶበታል።

ግሬት ፓሲፊክ ጋርቤጅ ፓች ከዓይን ዕይታ በላይ የሆነ በርካታ ቆሻሻ ተከምሮበት የሚታይ ሥፍራ ነው።

ሳይንቲስቶቹ ውቅያኖሶችን ከማፅዳትና የፕላስቲክ ምርቶችን መልሶ ከመጠቀም ይልቅ የሚመረተውን ፕላስቲክ መቀነሱ የተሻለ መፍትሔ ነው ብለው እንደሚያምኑ ቢቢሲ ዘግቧል።

# ስፖርት





## የባህል ስፖርቶችን ወደ ዓለም አቀፍ ደረጃ ለማሳደግ የተጀመረው ጥረት

**አስማየሁ ግዛው**

ዘመናዊ ስፖርቶች ከመስፋፋታቸውና ዛሬ ላይ ያላቸውን ቅርፅ ከመያዛቸው አስቀድሞ እንደየአካባቢው ባህላዊ የስፖርት ጨዋታዎችንና ውድድሮች ይካሄዱ ነበር። አንዳንድ ጥናቶችም ለበርካቶቹ ዘመናዊ ስፖርቶች የባህል ስፖርቶች መነሻ መሆናቸውን ይጠቁማሉ። የበርካታ ባህሎች ባለቤት በሆነችው ኢትዮጵያ የራሷ የሆኑ በርካታ ባህላዊ ስፖርቶች በተለያዩ አካባቢዎች ይከወናሉ፣ እየተከወኑም ይገኛሉ። እነዚህ ባህላዊ የስፖርት እንቅስቃሴዎች ከከተሞች መስፋፋት ጋር ተያይዞ ተዘውታሪነታቸው እየቀነሰ ሄዶ በገጠር አካባቢዎች ቢገደብም፤ በአገር አቀፍ ደረጃ እውቅና ተሰጥቷቸው በፌዴሬሽን እየተመሩ በየዓመቱ የባህል ፌስቴቫል እና ውድድር መድረኮች ይዘጋጃሉ።

በመጠናቀቅ ላይ ከሚገኘው ሳምንት መጀመሪያ አንስቶም አገር አቀፍ የባህል ስፖርት ውድድር ለ20ኛ ጊዜ እንዲሁም የባህል ፌስቲቫል ለ16ተኛ ጊዜ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በቤንች ሸኮ ዞን በሚዛን አማን ከተማ ሲካሄድ ቆይቷል። የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር፣ ከባህል ስፖርቶች ፌደሬሽን እና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ጋር በመተባበር ያዘጋጁት ይህ ውድድርም ‹‹የባህል ስፖርታችንና ፌስቲቫላችን ለአንድነታችን ለሰላማችን›› በሚል መሪ ሃሳብ ሲካሄድ ቆይቶ ወደ ማጠቃለያው ተቃርቧል። 9 ክልሎች እና ሁለት ከተማ አስተዳደሮች ተሳታፊ በሆኑበት ውድድርም፤ በ11 የባህል ስፖርቶች 884 ስፖርተኞች ተካፋይ መሆናቸው ታውቋል።

ተሳታፊዎች ከስፖርታዊ ውድድሮች ባለፈም የመጡበትን አካባቢ የሚገልጽ የጎዳና ላይ ባህላዊ ልብስ፣ ዘፈንና ውዝዋዜ በማሳየትም ውድድሩን አድምቀዋል።



**የኢትዮጵያን ባህላዊ ስፖርቶች ወደ ዓለም አቀፍ ደረጃ ለማሳደግ ጥረት እየተደረገ ነው፣**

የባህል ስፖርትና ጨዋታዎች ላይ ትኩረት ያደረጉና፤ የባህል ስፖርትና ጨዋታዎች ምንነት፣ አስፈላጊነት፣ ተግዳሮቶች እንዲሁም ስፖርቱን እንዴት ማሳደግ ይቻላል የሚሉ ዋና ዋና ሀሳቦች የተካተቱባቸው ጥናታዊ ጽሁፎችም ቀርበዋል።

እንደ ገና ጨዋታ ያሉ የባህል ስፖርቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ ከተለመደው የሆኪ ስፖርት ጋር ያላቸው ተመሳሳይነት በአገር ውስጥ ከመወሰን አልፎ በኦሊምፒክ እስከመሳተፍ የሚያደርስ መሆኑ ተጠቁሟል። የቀስት ውርወራና የፈረስ ጉግስም ቢሰራበት ጥሩ ውጤት ማምጣት እንደሚችልበት ይታመናል። በእነዚህ ስፖርቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ ተሳታፊ ለመሆን እቅድ ተይዞ ጥናቶችም ተጠንተው ወደ ትግበራ በመግባት ስፖርቱን ለማሳደግ መታቀዱን የባህል ስፖርቶች ፌዴሬሽን ጠቁሟል።

በባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የስፖርት ልማት መሪ ስራ አስፈጻሚ አቶ ተስፋዬ በቀለ፤ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ዓላማ አድርጎ የተቋቋመው የማህበረሰብ ስፖርትን ማስፋፋትና የስፖርት እንቅስቃሴን ማሳደግ መሆኑን ገልፀው፣ የማህበረሰብ የስፖርት እንቅስቃሴ ከሚባሉት የስፖርት ለሁሉም እንቅስቃሴዎች ጋር የባህል ስፖርትና የአካል ብቃት እንቅስቃሴን በማካተት ህብረተሰቡ በሚኖርበትና በሚሰራበት አካባቢ ጤንነቱን እንዲጠብቅ የተለያዩ ስራዎች እየተከናወኑ እንደሚገኙ ያብራራሉ።

በ1970 ዓ.ም በተደረገ ጥናት በኢትዮጵያ ያሉ የባህል ስፖርቶች 293 እንደሚደርሱ ይታወቃል። አሁን ግን ወጥ የሆነ ህግ ተረቆላቸው ውድድር የሚካሄድባቸው 11 ብቻ ናቸው። በቀጣይ ግን በየክልሉ ጥናት ተደርጎ ሁሉም ክልል በመረጠው የስፖርት ዓይነት ተሳታፊ እንደሚሆንም አቶ ተስፋዬ ይናገራሉ። እንደ ገና ያሉ ጨዋታዎችንም ከባህላዊ ስፖርትነታቸው ባሻገር ወደ ዘመናዊ ስፖርት ለማሳደግ ጥረት በመደረግ ላይ ነው። ውድድሩ በዓለም አቀፍ ደረጃ ትልቅ ቦታ የሚሰጠውና በኦሊምፒክ ከሚደረጉ ውድድሮች ጋር ተመሳሳይነት ስላለው ኢትዮጵያን በስፖርቱ ለመወከል ያስችላል ተብሎ ታምኖበታል። ይህንን ለማሳካት ግን አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ አስቀድሞ መስራት ተገቢ መሆኑን አቶ ተስፋዬ አስረድተዋል። ለአብነት ያህል የገና ጨዋታ (ሆኪ) ከአስራ አንድ በላይ ተጫዋችና የውድድር ቁሳቁሶች የሚፈልግ ውድድር በመሆኑ ብዙ ስራ ይፈልጋል።

ተወዳዳሪዎቹን ጨምሮ የማዘውተሪያ ስፍራውንና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮች ሲታከሉም ውድ ከሆኑ ስፖርቶች መካከል እንዲመደብ ያደርገዋል። ለዚህም መፍትሄ እንዲሆን የታሰበው ዓለም አቀፍ ስፖንሰሮችን ማፈላለግ እንደሆነም ስራ አስፈጻሚው ገልጸዋል። ለዚህም በስፖርቱ ጥሩ ደረጃ ላይ ከሚገኙ ሀገራት የሙያና ቁሳቁስ ድጋፍ ለማግኘት ጥረት እንደሚደረግ ተጠቁሟል። በተጨማሪም ስፖርቱን የሚያስተዋውቁ አሰልጣኞችንም ለማሰልጠን ዝግጅት እንደተጀመረ ተገልጿል።


### የሀራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

በፍርድ ባለመብት ወ/ሮ ዝናሽ ታከለ ወኪል ሙሉጌታ ይደነቃል እና የፍርድ ባለዕዳዎች እነ ተማሪ ተካልኝ ታከለ (2) ሰዎች መካከል ስላለው የአፈፃፀም ክርክር ጉዳይ ላይ የፍርድ ባለመብትና የፍርድ ባለዕዳዎች በውሳኔ መሰረት ለመካፈል ያልፈቀዱ ስለሆነ በሰሜን ሸዋ ዞን በጣ/በር ወረዳ በደ/ሲና ከተማ 01 ቀበሌ ልዩ ስሙ ቡርቸሌ ከተባለው ስፍራ በአዋሳኝ በምስራቅ ሸዋፈራ አየለ፣ ከምዕራብ ማሙሽ ከተማ፣ በሰሜን መንገድ እና በደቡብ ታደሰ መርድ መካከል የሚገኘውን በመነሻ ዋጋው 175102 ብር /አንድ መቶ ሰባ አምስት ሺ አንድ መቶ ሁለት ብር /መጋቢት 30 ቀን 2015 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡00 እስከ 6፡00 ሰዓት ንብረቱ በሚገኝበት በግልፅ ጨረታ ስለሚሸጥ ተጫራቾች /ወኪሎች ግምቱን 1/4 ለሀራጅ ባይ በማስያዝ ተጫርታችሁ መግዛት የምትችሉ ሲሆን ያስያዛችሁት ገንዘብ ለተሸናፊዎች የሚመለስ ሆኖ ለአሸናፊዎች ታሳቢ ሆኖ ገንዘቡን በ15 ቀን ውስጥ አጠናቀው ገቢ ማድረግ ያለባቸው መሆኑን ያሳውቃል፡፡

**የጣ/በር ወረዳ ፍ/ቤት**

### የንግድ ስራ ስለማፍረስ ማሳወጅ ማስታወቂያ

በባሌ ዞን በጎባ ከተማ በጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት ተደራጅተው ሲሰሩ ፈለቀች፣ እመቤት እና አታለለች ቡና እና ሻይ ስራ ሽርክና ማህበር በሚል እውቅና አግኝተው ንግድ ፍቃድ አውጥተው ሲሰሩ ቢቆዩም በደረሰባቸው ኪሣራ መሠረት ማህበሩን ለማፍረስ ስለተገደዱ እናንተም ይህንኑ አውቃችሁ ይህ ማህበር ህጋዊ በሆነ መንገድ የፈረሰ ሆኖ ተቃዋሚ ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ15 ተከታታይ ቀናት በጎባ ከተማ ኢንተርፕራይዞች እና ኢንዱስትሪ ልማት ጽ/ቤት እንዲቀርብ እናሳውቃለን።

**በባሌ ዞን የጎባ ከተማ የስራ ዕድል ፈጠራ እና ሙያ ጽ/ቤት**

### አማራ ክልል

ለወ/ሮ ሀድያ አድሴ በከሳሽ አቶ አማረ አራጋው እና በተከሳሽ ወ/ሮ አረጉ ሲሳይ መካከል ስላለው የመሬት ክርክር አስመልክቶ በቀረበው የመሬት ይለቀቅልኝ ክስ ክርክር ላይ ተከሳሽ መሬቱ የእኔ ሳይሆን የልጄ የሀድያ አድሴ ነው በማለት የገለፁ በመሆኑ ፍ/ቤቱ እርስዎ ተከሳሽን ተክተው እንዲከራከሩ ትዕዛዝ የሰጠ በመሆኑ በተለዋጩ ቀጠሮ መልስ አዘጋጅተው ለመጋቢት 21 ቀን 2015 ዓ.ም. እንዲቀርቡ በማለት የራያ ቆቦ ወረዳ ፍ/ቤት አዟል፡፡

**በአ.ብ.ክ.መ ጠቅላይ ፍ/ቤት የራያ ቆቦ ወረዳ ፍ/ቤት**

የባለንብረት ስም ጌታነህ አያሌው ዋሲሁን የተሽከርካሪው የሰሌዳ ቁጥር አማ-02-11227 የተሽከርካሪው አይነት ባለሁለት እግር ተሽከርካሪ ሞዴል PULSAR የተሽከርካሪው የአገልግሎት አይነት ለሰው የሞተር ቁጥር 68909 የሻንሲ ቁጥር 04574 የተሽከርካሪው የመጫን አቅም 1 ሰው በመሆኑም ሰሌዳውን ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይገቡዋለሁ የሚል ካለ በ15 ቀን የፍ/ቤት ማሳገጃ ይዞ እንዲቀርብ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን።

**በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ በምስ/ጎጃም ዞን መንገድና ትራንስፖርት መምሪያ የተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ቡድን**

### ለሁለተኛ ዙር የወጣ የሰርቨር ግዥ ጨረታ ማስታወቂያ

የሆለታ ከተማ ገንዘብና ጽ/ቤት ለ2015 በጀት ዓመት ለመሬት አስተዳደር ለክላስተር ስራ የሚውል የሰርቨር በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡

**ስለዚህ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርት የምታሟሉ ነጋዴዎች መወዳደር ትችላላችሁ፡፡**

1. በዘርፉ ህጋዊ ንግድ ፈቃድ ኖሮት የታደሰ የንግድ ፈቃድ የያዘና የዘመኑን ግብር የከፈለ፤
2. በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በአቅራቢነት ዝርዝር የተመዘገበና ሰርተፍኬት ያለው፤
3. ተጫራቾች ካወጣችሁት ንግድ ስራ ዘርፍ ውጪ የተወዳደረ ተጫራች ከጨረታው ይሰረዛል።
4. ለጨረታ ማስከበሪያ በባንክ የተረጋገጠ 50000 ብር በሲፒኦ /በቼክ ማስያዝ የሚችልና ጨረታውን ካሸነፈ ለውል ማስከበሪያ ያሸነፈበትን ዕቃ ጠቅላላ ዋጋ 10 /100 በባንክ ማስያዝ የሚችል፤
5. ተጫራቹ ጨረታውን ካሸነፈ ዕቃዎቹን በራሱ ወጪ እስከ ሆለታ ከተማ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት ማቅረብ የሚችል፤
6. መስሪያ ቤቱ ለሚጠረጥራቸውና ማጣራት ለሚፈልገው ዕቃ ናሙና ማስቀረብ ይችላል፤
7. ጨረታው ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ15 ተከታታይ የስራ ቀናቶች በአየር ላይ የሚቆይ ሲሆን በ16ኛው በ8፡00 ሰዓት ላይ የሚጠናቀቅ ሲሆን በዚሁ ቀን በ8፡30 ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ተወካዮቻቸው በተገኙበት በግልጽ ይከፈታል።
8. ተጫራቾች የጨረታውን ሰነድ በማይመለስ 500 ብር ከሆለታ ከተማ ገንዘብ ጽ/ቤት በንግድ ባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000015721646 በማስገባት ቢሮ ቁጥር 1 በመምጣት ሰነድ መግዛት ትችላላችሁ፡፡

**ማሳሰቢያ**፦ መስሪያ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

**ለበለጠ መረጃ ስልክ ቁጥር**

0112370095፣0911045695፣ 0913445227፤ 0922203464፤0913469364፤ 0913753822 መጠየቅ ትችላላችሁ፡፡

**በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት**

**ሆለታ ከተማ አስተዳደር ገንዘብ ጽ/ቤት**